# ኢትዮ ቻምበር

ሚዲያ ጭማቂ

በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት

በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኮሚኒኬሽንና ህዝብ ግንኙኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ ወርሃዊ የሚድያ ጭማቂ

መስከረም 2014 ዓ.ም.



ም/ዋና ፀሀፊው የካዛኪስታን አምባሳደርን- 2

የአልጀርስ ኩባንያ ከፍተኛ ሀላፊዎች - 2

የዋጋ ግሽበትን መቀነስ የመንግሥት - 2

የሚኒስሮች ምክር ቤት በገቢ ግብር -3

አዲስ የአፍሪካ-አሜሪካ ዲያስፖራ - 3

በኢትዮጵያ የአሜሪካ ንግድ ምክር - 4

በንግድ ዘርፉ ተዋናዮች ላይ - 4

ባህር ትራንስፖርት 10 ሚሊዮን- 5

ብሔራዊ ባንክ የግምጃ ቤት - 5

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሰባት - 5

የንግዱ ማህበረሰብ እና አምራቾች- 6

መቀመጫቸውን ጅቡቲ ያደረጉ- 6

በአራተኛው የንግድ ትርኢት ላይ - 6

የኤክስፖ 2020 ዱባይ የኢትዮጵያ - 6

የቆዳ ሃብትን በአግባቡ ለመጠቀም - 7

የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ - 7

ለኢትዮጵያ ባንኮች አፍሪ ኤግዚም - 7

የኢትዮጵያና ኬኒያ የሞያሌ አንድ ድንበር - 8

በተያዘው በጀት ዓመት የገበያ ማረጋጋት- 8

ኮሚሽኑ በአሸባሪው ህወሓት የወደሙ - 8

የኢትዮ–ኬንያ በኢነርጂ ዘርፍ ላይ - 8


## ምክር ቤቱ የነጩ ፖስታ ጎርፍ ለነጩ ቤተ መንግስት ሀገራዊ ንቅናቄን አስጀመረ






የነጩ ፖስታ ጎርፍ ለነጩ ቤተ መንግስት ሀገራዊ ንቅናቄ የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት፣ አመራሮችና ሰራተኞች በተገኙበት በምክር ቤቱ የ መሰብሰቢያ አዳራሽ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም ተጀመረ፡፡

በስነ ስርአቱ ላይ የተገኙት የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት ኢንጂነር መላኩ እዘዘው እንደገለጹት ይህ "የነጩ ፖስታ ጎርፍ ወደ ነጩ ቤተ-መንግስት" በሚል መሪ ቃል የሚካሄደው ሀገራዊ ንቅናቄ ዓላማ ን ከግቡ ለማድረስ የግሉዘርፍ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከአሜሪካ ጋር ያላት የንግድ እና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ዘመናትን የተሻገረ መሆኑን ያነሱት ፕሬዚደንቱ የአሜሪካ መንግስት በሰጠው አህጉራዊው ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት 'አጎአ' (AGOA) ተጠቃሚነታችን የሚጠበቀውን ያህል ባይሆንም ፤ በየጊዜው እየተስፋፉ ባሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እንዲሁም በኢኮኖሚ ማሻሻያ ርምጃዎች ምክንያት እየጎለበተ የመጣ ሲሆን ፤ አሰራሩ ከምንጊዜውም በተሸለ መልኩ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል የሚል ጠንካራ እምነት አለን ብለዋል፡፡

አያይዘውም በአገራችን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በተከሰቱ ግጭቶች መነሻ የአሜሪካ መንግስት ለታዳጊ አገራት የሰጠው ይህ እድል ለኢትዮጵያ እንዲነፈጋት የሚወተውቱ አካላት ከድርጊታቸው መቆጠብ እንደሚገባቸው ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም በዚህ የነጩ ፖስታ ጎርፍ ለነጩ ቤተ መንግስት ሀገራዊ ንቅናቄ የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ተሳትፎ ማድረጉን ወቅታዊና አስፈላጊ ያደርገዋል ብለዋል፡፡

በመሆኑም መላው የንግዱ ማኅበረሰብ የኢትዮጵያን እውነታ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለማሳወቅ በሚደረገው በዚህ ሀገራዊና ጥረት ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግም ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በዚህ ሀገራዊ ንቅናቄ መድረክ ከምክር ቤቱ ፕሬዚደንት በተጨማሪ ዋና ጸኃፊው አቶ የሱፍ አደምኑር እንዲሁም ሌሎች ሰራተኞችና አመራሮችም ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

እንደሚታወቀው በንቅናቄው ከአምስት ሚሊዮን በላይ የህብረተሰብ ክፍሎች ፊርማቸውን በማሰባሰብ የነጭ ፖስታ ጎርፍ ወደ አሜሪካው ነጩ ቤተ መንግስት የሚላክ ሲሆን፤ በመላ ሀገሪቱ ያሉ ዜጎች ፤ አለም አቀፉ ማህበረሰብ የኢትዮጵያን እውነታ እንዲረዳ፣ ከጣልቃ ገብነት እንዲታቀብ መልዕክት ለማስተላለፍ ታስቦ እየተካሄደ ያለ አገር አቀፍ ዘመቻ ነው፡፡

## ዋና ፀሀፊው የባንግላድሽን አምባሳደር ተቀብለው አነጋገሩ

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ዋና ፀሀፊ አቶ የሱፍ አደምኑር በኢትዮጵያ የባንግላድሽ አምባሳደር ናዝሩል ኢስላምን መስከረም 4 ቀን 2014 ዓ.ም በፅ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ፡፡

አምባሳደር ናዝሩል ኢትዮጵያ እና ባንግላድሽ የረጅም ጊዜ ወዳጅነት ያላቸው አገሮች መሆናቸውን በመጥቀስ ኢትዮጵያ በተለይም የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ በመሆኗ ዘርፈ-ብዙ ግንኙነት ከማድረግ ረገድ በጣም አስፈላጊ አገር መሆኗን ተናግረዋል፡፡ ንግድና ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ በመንግስት በኩል በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ካልተጨመረበት የታቀዱ ስራዎች ግባቸውን አንደማይመቱም ብለዋል፡፡ አያይዘው የባንግላድሽ እና የኢትዮጵያን የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከርና ለማሳደግ በሁለቱ አገሮች ንግድ ምክር ቤቶች መካከል የመግባቢያ ስምምነቶች ማድረግ እና ስራዎችን በትብብር መስራት እንሚገባ አክለዋል፡፡ የባንግላድሽ ባለሀብቶች በጨርቃጨርቅ፣ በግብርና እና በመድሀኒት ማምረት ዘርፎች መሰማራት እንደሚፈልጉም አምባሳደሩ ጠቁመዋል፡፡

የምክር ቤቱ ዋና ፀሀፊ አቶ የሱፍ በበኩላቸው ምክር ቤቱ የንግድና ኢንቨስትመንትን እንደሚያስፋፋ፣ የአቅም ግንባት ስልጠናዎችን እንደሚሰጥ፣ የምርምርና አድቮኬሲ ስራዎችን በመስራት እና የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የውይይት መድረኮችን በማካሄድ በየጊዜው የሚጋጥሙ የቢዝነስ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እንደሚያደርግ አስረድተዋል፡፡ ለንግዱ ማህበረሰብ ልዩ ልዩ ጠቃሚ የቢዝነስ መረጃዎችን በማሰራጨት፣ በቢዝነስ እንቅስቃሴ ወቅትም የሚያጋጥሙ ግጭቶችን በምክር ቤቱ የዳኝነት ግልግል ማዕከል በኩል በመፍታት የንግድ እና ኢንቨስትመንቱን ከባቢ ምቹ ከማድረግ አኳያ ምክር ቤቱ በርካታ ተግባራትን እንደሚያከናውንም አብራርተዋል፡፡ በሁለቱ አገሮች በርካታ የንግድና ኢንቨስትመንት ሀብቶች መኖራቸውን ጠቅሰው



የባንግላድሽ ባለሀብቶች ኢትዮጵያ መጥተው በማንኛውም ዘርፍ ቢሰማሩ ተጠቃሚ እንደሚሆኑም ተናግረዋል፡፡ ምክር ቤቱ በቀጣይ ከባንግላድሽ አቻው ጋር የመግባቢያ ስምምነቶችን በማድረግ የሁለቱን አገራት ንግድና ኢንቨስትመንት የሚያሳድጉ ተግባራትን በትብብር ለመስራት ዝግጁ እንደሆነም ዋና ፀሀፊው አክለው ገልፀዋል፡፡

## ም/ዋና ፀሀፊው የካዛኪስታን አምባሳደርን አነጋገሩ



የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ፀሀፊ አቶ ውቤ መንግስቱ በኢትዮጵያ የካዛኪስታን አምባሳደር ባርሊቤይ ሳዲኮቭን ተቀብለው ሁለቱ አገራት የንግድና የኢኮኖሚ ግንኙነታቸውን በሚያጠናክሩበትና በትብብር በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ዙሪያ አነጋገሩ፡፡

አምባሳደሩ በሁለቱ አገራት መካከል ያለው የንግድና ኢኮኖሚ ትስስር እና ትብብር አነስተኛ መሆኑን በማስታወስ በቀጣይ ግንኙነታቸውን ለማጠናከርና ለማሳደግ እንደሚፈለጉ ተናግረዋል፡፡ አያይዘውም የንግዱ ማህበረሰብ እርስ በርስ ግንኙነት የሚፈጥሩበት እና ስለ ሁለቱ አገራት የንግድና ኢንቨስትመንት እምቅ ሀብቶችና እድሎች በቂ መረጃና የእውቀት ልውውጥ የሚያገኙበት መድረክ ማመቻቸት አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

የምክር ቤቱ ም/ዋና ፀሀፊ በበኩላቸው ሰለምክር ቤቱ አመሰራረት፣ አደረጃጀትና የሚያከናውናቸውን ዋና ዋና ተግባራት በመግለፅ በአገሪቱ የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን ምቹ ከማድረግ አኳያ የሚያጋጥሙ መሰናክሎችና ችግሮችን ለመፍታት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ በተዋረድ ከሚገኙ አጋር አካላት ጋር ምክር ቤቱ መድረኮችን በማዘጋጀት በየጊዜው ውይይት እንደሚያደርግ አስረድተዋል፡፡ በኢትዮጵያ አንዳንድ አገሮችም የቢዝነስ ካውንስል እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡ ኢምባሲው የሁለቱ አገራት የንግድ ማህበረሰብ የሚገናኙበትና በቂ የቢዝነስ መረጃ የሚለዋወጡበትን መንገድ ከማመቻቸት ረገድ እንዲሁም የሀገራቱን የንግድና የኢኮኖሚ ትብብር ለማሳደግ ያሳየውን ተነሳሽነት በማመስገን በቀጣይ በሚያዘጋጀው የቢዝነስ ሴሚናር ምክር ቤቱ አብሮ እንደሚሰራና አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ እንደሚያደርግ ም/ዋና ፀሀፊው አክለው ገልፀዋል፡፡

## የአልጀርስ ኩባንያ ከፍተኛ ሀላፊዎች ከኢትዮጵያ አቻቸው ጋር የቢዝነስ ትስስር አደረጉ




የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጂአይኤስቢ(GISB) የተሰኘ የአልጀርስ ኩባንያ ከፍተኛ ሀላፊዎችን እና በኢትዮጵያ በኬብል እና በፕላስቲክ ማምረቻ ዘርፍ የተሰማሩ አምስት የግል ኩባንያዎች የስራ ሃላፊዎችን መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም በምክር ቤቱ የስልጠና አዳራሽ ተቀብሎ የአቻ ለአቻ የቢዝነስ ትስስር (Business Networking) እንዲፈፅሙ አደረገ፡፡

ሁለቱ ወገኖች ኩባንያዎቻቸዉ ስለሚያቀርቡት ምርትና አገልግሎት፣ ስለሀገሪቱ የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች እንዲሁም በቀጣይ በጋራ ስለሚሰሩባቸው ጉዳዮች መረጃ ተለዋውጠዋል፡፡

ጂአይኤስቢ(GISB) የተሰኘው ኩባንያ የኤሌትሪክ ኬብሎችንና ትራንስፎርመሮችን በማምረት በአልጀርስ ከፍተኛ ድርሻ ያለው እና በኢትዮጵያም በኢንቨስትመንት መሰክ ለመሰማራት ፍላጎት ያሳየ ኩባንያ መሆኑ ታውቋል፡፡

## የዋጋ ግሽበትን መቀነስ የመንግሥት ዋነኛ ትኩረት እንደሚሆን ተገለጸ




ቀጣዮቹን አምስት ዓመታት አገሪቱን ለመምራት የተመሠረተው መንግሥት የዋጋ ግሽበትን መቀነስ ዋነኛ ትኩረቱ እንደሚሆን አስታወቀ፡፡

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ወ/ሮ ሳህለወርቅ ዘውዴ መስከረም 24 ቀን 2014 ዓ.ም. ለአዲሶቹ የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አባላት ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንዳስታወቁት፣ በኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የአገሪቱን ማክሮ ኢኮኖሚ በማረጋጋት የተጀመረው ዕድገት ወደኋላ ሳይመለስ እንዲቀጥል ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡

የሥራ ዕድል በማስፋፋት የተንሰራፋው ሥራ አጥነት እንዲቃለል ጥረት እንደሚደረጉ የገለጹት ፕሬዚደንቷ፣ ከሁሉም በላይ የዋጋ ግሽበቱን በመቀነስ የኑሮ ውድነት እንዲስተካከልና በተፈጥሯዊና በሰው ሠራሽ ተግዳሮቶች የገጠሙ ጉድሎቶችን በፍጥነት በማረም፣ ሁለንተናዊ ዕድገት እንዲረጋገጥ መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል ብለዋል፡፡

በአገሪቱ እየጨመረ ለመጣው የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት መንስዔ የሆኑት የአቅርቦትና የፍላጎት አለመመጣጠን፣ ዝናብን መሠረት ያደረገ የግብርና ሥርዓት፣ የተዛባ የንግድ ሥርዓት ለማስተካከል በትኩረት እንደሚሠራ፣ የኑሮ ውድነቱን በዘላቂነት ለማቃለል የገንዘብና የፊስካል ፖሊሲ ቁጥጥር ሥራ አፅንኦት እንደሚሰጠውና የንግድ ሥርዓቱን የማስተካከል ሥራ የዚህ ዓመት የትኩረት አቅጣጫ ይሆናል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር) መስቀል አደባባይ በተካሄደው የመንግሥት ምሥረታ ንግግር፣ አዲስ የተመረጠው መንግሥት የቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ ከሚሠራባቸው የኢኮኖሚ አስተዳደር ሥራዎች መካከል አንዱ የዋጋ ንረትን መግራት ይሆናል ብለዋል፡፡

የመንግሥት ገቢን በ2014 ዓ.ም. 600.9 ቢሊዮን ብር ለማድረስ ግብ የተጣለ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 83 በመቶ የሚሆነው ገቢ ከታክስ ለመሰብሰብ መታቀዱ በፕሬዚደንቷ ንግግር ተመላክቷል፡፡ በ2014 የበጀት ዓመት ጠቅላላ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ 5.25 ቢሊዮን ዶላር እንዲደርስ መታቀዱን ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ያስረዱ ሲሆን፣ በግብርና መስክ ደግሞ 592 ሚሊዮን ኩንታል የሰብል ምርት ለማምረት ዕቅድ እንደተያዘ ጠቁመዋል፡፡

ማኑፋክቸሪንግን በተመለከተ የነባር አምራቾችን ምርትና ምርታማነት በማሻሻል፣ እንዲሁም ጥራት ያላቸውን አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ ዘርፉ ለሥራ ዕድል ፈጠራ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት በትኩረት ይሠራል ተብሏል፡፡

ስትራቴጂካዊ የሆኑ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ የማኑፋክቸሪንግ ውጤቶች እንዲስፋፉ እንደሚደረግና የወጪ ንግድ ምርቶችን በብዛት፣ በጥራትና በዓይነት ማምረት፣ የአገር ውስጥ ባለሀብቱ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ በስፋት እንዲሰማራ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ኢንዱስትሪው ለጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚያደርገውን አስተዋፅኦ ማሳደግ፣ ንዑስ ዘርፉንም ከአገሪቱ ዘላቂ ልማት፣ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ ለማድረግ እንደሚሠራ ተመላክቷል፡፡

ፕሬዚደንት ሳህለወርቅ በንግግራቸው ማዕድናትን በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ለገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ የውጭ ምንዛሪ ግኝት እንዲያደርጉ በብርቱ ይሠራል ያሉ ሲሆን፣ ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ማዕድናት በአገር ውስጥ እንዲቀርቡ እንደሚደረግ፣ ከፍተኛ የማዕድናት ሀብት ባለባቸው አካባቢዎች የሚስተዋሉ የፀጥታ ችግሮች እንዲቀረፉ በልዩ ትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡ በዘርፉ የተማራ የሰው ኃይል ልማት በጥራትና በብዛት እንዲኖር ከማድረግ በሻገር፣ ለባህላዊና ለአነስተኛ የማዕድን አምራቾችም ልዩ ትኩረት እንደሚሰጥ አስታውቀዋል፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አገራዊ አቅም በመገንባት አብዛኛው የአገር ውስጥ ፍላጎት በአገር በቀል ኩባንያዎች እንዲሸፈን ይደረጋል ያሉት ፕሬዚደንቷ፣ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጥርና የኮንስትራክሽን ግንባታዎች የጥራት፣ የወጪና የጊዜ ተወዳዳሪነትን ማሻሻል እንደሚያስፈልግ አስምረውበታል፡፡

የመንገድ መሠረተ ልማትን የተቀናጀ፣ ፍትኃዊና ተደራሽ በማድረግ የከተሞች ልማትና የገጠር ዕድገትን የሚያፋጥን እንቅስቃሴ በከተማና በገጠር በተመጋጋቢ መንገድ በመተግበር የከተማ ምጣኔ ያድጋል የተባለ ሲሆን፣ ከተሞች በተሟላ ዕቅድና በተማከለ የከተማ አስተዳደር እንዲመሩ ከማድረግ በተጨማ የከተሞችን የመሬትና የመኖሪያ ቤት አቅርቦትና አስተዳደር ሥርዓት ውጤታማነትን በማሻሻል ምቹ የመኖሪያ አከባቢ ለመፍጠር እንደሚሠራ ተገልጿል፡፡

ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘውን ሀብት ለማሳደግ የቅርስ እንክብካቤና ጥበቃ ሥራ በማጠናከር የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ በማሻሻል ነባር መዳረሻዎችን ማጎልበት ይገባል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፣ በተጨማሪም አዳዲስ የቱሪስት መስህቦች እንዲለሙ ከማድረግ ባሻገር፣ በገበታ ለአገር ፕሮጀክት የተጀመሩ የጎርጎራ፣ የወንጪና የኮይሻ የቱሪስት መዳረሻ ልማቶች በዕቅዳቸው መሠረት ክንውናቸው እንዲቀጥል ይደረጋል ብለዋል፡፡

በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተጀመሩና ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን በተያዘው ዓመት በማጠናቀቅ ለሕዝብ ጥቅም እንዲውሉ እንደሚደረግ፣ የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ኃይጅን አቅርቦትን በማስፋፋት የአገልግሎቱ ተደራሽ ያልሆነውን ሕዝብ ተጠቃሚ እንደሚደረግና ንፁህ ኢነርጂና ቴክኖሎጂ ለገጠሩ ኅብረተሰብ እንዲዳረስ፣ ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት እንዲቀርብ በትኩረት እንደሚሠራ በፕሬዚደንቷ ንግግር ተመላክቷል፡፡

በሌላ በኩል የሚታለሙትና እንደ ግብ የሚቀመጡት በጎ ዓላማዎች ትርጉም የሚኖራቸው ባለው የማስፈጸምና የማድረግ አቅም ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ ደግሞ አዲሱ መንግሥት የሚያስብ፣ የሚያቅድና የሚከውን እንጂ በጎ የሚመኝና ህልመኛ ብቻ ሊሆን እንደማይገባ በመግለጽ፣ «እስከ ዛሬ ታቅደው ከጠረጴዛ ላይ ያልወረዱና ተጀምረው የተሰናከሉ ውጥኖች ባለንበት የምንረግጥና አንዳንዴም ወደኋላ የምንሸራተት እንድንሆን አድርገውናል፤» ብለዋል፡፡

በዜጎች ላይ የሚደርሰውን ምሬትና መንገላታት ለመቅረፍ፣ ጀምሮ የመጨረስን ባህል በመላበስ በቴክኖሎጂ የታገዘ ግልጽና ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥና ምቹ የሕዝብ አስተዳደር እንዲኖር አበክረን እንሠራለን ያሉት ዓብይ (ዶ/ር)፣ በተለይ ሌብነትን እንደ ቀላል ድክመት ሳይሆን እንደ ከፍተኛ የደኅንነትና የህልውና አደጋ በማየት፣ በቀጣዩ ዓመታት ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ አስታውቀዋል፡፡

የኢኮኖሚ ምሁራን የዋጋ ግሽበትንና የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ መከናወን ይገባቸዋል የሚሉ ምክረ ሐሳቦችን ይሰነዝራሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ መንግሥት ሰላምና መረጋጋትን በመፍጠር ሥጋት በማስወገድ ማኅበረሰቡ የተረጋጋ ኑሮ እንዲኖር ማድረግ፣ በከተሞች አካባቢ በዕቅድ የሚመራ የምርቶች አቅርቦት ሊኖር እንደሚገባ፣ የአምራቾችና የሸማቾች ማኅበራት በመንግሥትና በሌሎች ባለድርሻ አካላት መጠናከር እንዳለባቸው፣ መንግሥት ሕገወጥ ነጋዴዎችን የሚቆጣጠርበት ሥርዓት ማበጀት እንደሚገባውና የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ለበለጠ መረጃ፤

https://www.ethiopianreporter.com/article/23375

# የሚኒስሮች ምክር ቤት በገቢ ግብር ደንብ ላይ ያደረጋቸው ማሻሻያዎች

የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባው ከተመለከታቸው ጉዳዮች መካከል በሥራ ላይ የሚገኘው የገቢ ግብር ደንብ ይገኝበታል፡፡

የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ከነሐሴ ወር 2009 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሥርዓትን ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ፣ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በተገቢው መንገድ በመምራት ተገቢውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማስገኘት ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የገቢ ግብር ደንቡ አንዳንድ አንቀጾች ግልጽነት የጎደላቸውና በተወሰኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች እንቅስቃሴ ላይ ጫናን እያሳደሩ መሆኑ በመታወቁ፣ በተለዩት በእነዚህ ደንቦች ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ ተጠይቋል፡፡

የቀረበውን ማሻሻያ የተለከተው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማሻሻያውን ተቀብሎ ያፀደቀ ሲሆን፣ የተደረጉት ማሻሻያዎችን በተመለከተ ሪፖርተር በሚከተለው ሁኔታ አቅርቦታል፡፡

በገቢ ሰብሳቢው ተቋምና በግብር ከፋዮች መካከል የውዝግብ ምንጭ እንዲሁም በኢንቨስትመንት ላይ ጫና በማሳደራቸው ማሻሻያ እንዲደረግባቸው የተወሰነባቸው አንቀጾችና ማሻሻያዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የካፒታል ዕቃዎች የኪራይ ውል (አንቀጽ 34)

በካፒታል ዕቃ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 እንደተደነገገው ሦስት ዓይነት የካፒታል ዕቃዎች የኪራይ ውል ያለ ሲሆን፣ እነዚህም የፋይናንስ ኪራይ፣ የአጭር ጊዜ የመጠቀሚያ ኪራይና የዱቤ ግዥ ናቸው፡፡

በፋይናንስ ኪራይና በአጭር ጊዜ የመጠቀሚያ ኪራይ የንብረቱ ባለቤት አከራይ ሲሆን፣ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት መሠረት በውሉ ዘመን መጨረሻ የንብረቱ ባለቤትነት ወደ ተከራዩ ሊተላለፍ ይችላል፡፡ በዱቤ ግዥ ውል ግን ገዥው በከፈለው ገንዘብ መጠን የንብረቱ ባለቤት የሚሆን ሲሆን ዕዳውን ከፍሎ ሲያጠናቅቅ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ሙሉ በሙሉ የንብረቱ ባለቤት ይሆናል፡፡

ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 አንቀጽ 16 የዱቤ ግዥ ስምምነትን በሚመለከት የእርጅና ቅናሽ የሚታሰበው ለተከራዩ መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ በገቢ ግብር ደንብ አንቀጽ 34(1) በሦስቱም ዓይነት የካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ውል ተከራዩ የከፈለው የኪራይ ክፍያ ከጠቅላላ የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተቀናሽ የሚደረግና ለተከራዩ የእርጅና ቅናሽ የማይታሰብ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በዚህም ምክንያት የካፒታል ዕቃዎችን በዱቤ ግዥ ውል በመከራየት ሥራቸውን የሚያከናውኑ አነስተኛና ጥቃቅን ድርጅቶች ለንብረቱ ዋጋ ያወጡት ወጪ በአጭር ጊዜ ውስጥ በወጪ ተቀናሽ እንዲሆንላቸው የሚያስችለው የእርጅና ቅናሽ ተጠቃሚ ባለመሆናቸው ሥራ በጀመሩባቸው ዓመታት ከፍተኛ ግብር እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ፡፡

ይህንን ችግር ለማቃለል የገቢ ግብር ደንቡ ከካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲቀረፅ ተደርጓል፡፡ በከፊል ለንግድ ሥራ በዋለ ሕንፃ ላይ የሚታሰብ የእርጅና ቅናሽ (አንቀጽ 40) በሕንፃ ሥራ አዋጅ የተደነገገውን በመከተል እንዲሁም ለታክስ አስተዳደር ያለውን አመቺነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሕንፃ የእርጅና ቅናሽ የሚፈቀደው የሕንፃው ግንባታ ከተጠናቀቀ በኋላ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ ከተጠናቀቀ በኋላ በከፊል ለንግድ ሥራ በከፊል ደግሞ ለሌላ አገልግሎት ስለሚውል ሕንፃ የሚደነግገውን የደንቡን አንቀጽ 40 ሙሉ በሙሉ ሳይጠናቀቅ ለኪራይ የዋለ ሕንፃ ላይ የእርጅና ቅናሽ እንዲሰላ የሚፈቅድ አንቀጽ እንደሆነ በመቁጠር ያለመግባባት ይፈጠራል፡፡

ይህንን ውዥንብር ለማጥራት አንቀጹ የሚመለከተው ሙሉ በሙሉ ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ በከፊል ለንግድ ሥራ የዋለን ሕንፃ መሆኑ በግልፅ እንዲመለከት ተደርጓል፡፡

ኪሣራን ስለማሸጋገር (አንቀጽ 42(1))

አንድ ግብር ከፋይ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ባለበት ጊዜ ሊካካስለት የሚችለው ሁለት ጊዜ ያጋጠመ ኪሳራ እንደሆነና ይህም ኪሳራ የሚሸጋገረው ቢበዛ ለአምስት ዓመታት ጊዜ እንደሆነ በገቢ ግብር አዋጁ ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ ግብር ከፋዩ ኪሳራውን ለማካካስ የሚችለው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ሲኖረው በመሆኑ በአምስቱ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያጋጠመውን ኪሳራ ማካካስ የሚያስችል ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከሌለው ኪሳራው ከአምስት ዓመት በላይ ሊሸጋገር ይገባል የሚል ክርክር ይነሳል፡፡

በንግድ ሥራ ውስጥ ያለ ግብር ከፋይ ላልተወሰነ ጊዜ ኪሳራ እያጋጠመው በሥራው ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ስለማይችል አዋጁ ሊካካስ የሚችለው ሁለት ጊዜ ያጋጠመ ኪሳራ ሆኖ በአምስት ዓመት ውስጥ መሆኑን በግልፅ የደነገገ ሆኖ ሳለ ለአንቀጹ የሚሰጠው ትርጉም የተሳሳተ ነው፡፡

ይህንን ግልጽ ለማድረግ በአምስቱ ዓመት ውስጥ ግብር ከፋዩ ቀድሞ ካጋጠመው የሁለት ጊዜ ኪሳራ በላይ ተጨማሪ ኪሳራ አጋጥሞኛል የሚል የገቢ ማስታወቂያ የሚያቀርብ ከሆነ ኪሳራው ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ ሊሸጋገር የማይችል መሆኑ ግልፅ ተደርጓል፡፡



የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሳራ

በገቢ ግብር ደንቡ አፈጻጸም ረገድ አስቸጋሪ ከነበሩት ድንጋገዎች አንዱ የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሳራን የሚመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ ከባንኮች ውጪ ያሉ ሌሎች የንግድ ሥራ ድርጅቶች ለካፒታል ንብረት ማፍሪያ የወሰዱትን ብድር በሚከፍሉበት ወይም በውጭ ምንዛሪ ሌሎች የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎችን በሚያከናውኑበት ጊዜ የውጭ ምንዛሪ ኪሳራ ያጋጥማቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የገቢ ግብር ደንቡ በውጭ ምንዛሪ ግብይት የደረሰ ኪሳራ ሊካካስ የሚችለው በውጭ ምንዛሪ ግብይት ከተገኘ ጥቅም ጋር ብቻ እንደሆነ ስለሚደነግግና እነዚህ ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ የማይዙ በመሆኑ ከግብይቱ የሚያገኙት ጥቅም ስለሌለ ለከፍተኛ ችግር ሲዳረጉ ቆይተዋል፡፡

ይህንን ችግር ለማቃለል በውጭ ምንዛሪ ግብይት ያጋጠመ ኪሳራ ለሁለት ተከፍሎ፣ ማሻሻያ እንዲደረግበት ተወስኗል፡፡

በዚህም መሠረት አንደኛ፣ የውጭ ምንዛሪ ግብይቱ የተፈጸመው ከካፒታል ንብረት ግዥ ጋር በተያያዘ ከሆነ ኪሳራው የካፒታል ንብረቱ የተገዛበት ዋጋ ላይ ተደምሮ ለእርጅና ቅናሽ መሠረት እንዲሆን፣

የውጭ ምንዛሪ ግብይቱ የተፈጸመው ከካፒታል ንብረቱ ግዥ ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ ከሆነ ኪሳራው በግብር ዘመኑ እንደ ወጪ እንዲያዝ፣ በሚያስችል አኳኋን አንቀጹ ተሻሽሏል፡፡

የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር (አንቀጽ 56(1))

የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር የሚከፈለው ለንግድ ሥራ የተያዘን ሕንፃ ወይም አክሲዮንን በማስተላለፍ በሚገኝ የዋጋ ዕድገት ጥቅም ላይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የገንዘብን የመግዛት አቅም መቀነስ ተከትሎ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ እንዲደረግ የገቢ ግብር ደንቡ የሚፈቅደው ለህንፃ ብቻ በመሆኑ፣ አክሲዮን የሚሸጡ ግብር ከፋዮች የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ሳይደረግ የአክሲዮን ሰነዱ ላይ በተፃፈው ዋጋ (Par Value) እና በተሸጠበት ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት ጥቅም እንደሆነ ተቆጥሮ ግብር እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ፡፡

ይሁን አንጂ በገቢ ግብር አዋጁ እንደተመለከተው ግብር ከፋዩ በትክክል አግኝቷል ሊባል የሚችለው ጥቅም በአክሲዮኑ የወቅቱ ዋጋና በተሸጠበት ገንዘብ መካከል ያለው ልዩነት ስለሆነ ከአክሲዮን ሽያጭ ለሚገኝ የዋጋ ዕድገት ጥቅምም የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ እንዲፈቀድ በሚያስችል አኳኋን አንቀጹ ተሻሽሏል፡፡

ተካከሶ ያልተጠናቀቀ ኪሳራ (አንቀጽ 68)

ግብር ከፋዮች ቀደም ሲል በሥራ ላይ በነበረው አዋጅ ሁለት ኪሳራ የተካካሰላቸው ቢሆንም በአዲሱ አዋጅ መሠረት ተጨማሪ ሁለት ኪሳራ ሊካካስላቸው እንደሚገባ ይጠይቃሉ፡፡

በመሆኑም ለዚህ ጥያቄ መሠረት የሆነው ግልፅነት የጎደለው አንቀጽ እንዲሻርና ሊካካስ የሚችለው ከሁለት ዓመት ኪሳራ ውስጥ ያልተካካሰው ቀሪ መጠን ብቻ መሆኑ ግልፅ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የደንቡ ተፈፃሚነት

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የደንቡ ድንጋጌዎች ጋር በተያያዘ በተፈጠረ ያለመግባባት በርካታ ጉዳዮች ውሳኔ ሳያገኙ በእንጥልጥል ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ችግሩን ወጥ በሆነ መልኩ ለመፍታት ክፍያ ያልተፈጸመባቸው ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ የግብር ጉዳዮች በዚህ ደንብ መሠረት ፍጻሜ የሚያገኙ መሆኑን የሚገልፅ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ለበለጠ መረጃ፤

https://www.ethiopianreporter.com/article/23321

# አዲስ የአፍሪካ-አሜሪካ ዲያስፖራ ኢኒሼቲቭ ትብብር ይፋ ሆነ

የቡና አምራች አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚያስችል አዲስ የአፍሪካ-አሜሪካ ዲያስፖራ ኢኒሼቲቭ ይፋ ሆነ።

ኢኒሼቲቩ ቤኔፊት ኮርፖሬሽን ፎር አፍሪካ አሜሪካ የሚባል ሲሆን የአፍሪካና አሜሪካን ግንኙነት ከልመና ይልቅ በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያስችል ነው ተብሏል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዶኤታ አምባሳደር ምስጋና አረጋ ኢትዮጵያ ባላት የቡና ምርት ልክ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ተጠቃሚ ባለመሆኗ ኢኒሼቲቩ ቡና አምራቹን አርሶ አደር ከመጥቀሙ ጎን ለጎን አገሪቱ በዓለም ዐቀፍ ገበያው ተወዳዳሪ እና ብቁ እንድትሆን ያስችላታል ብለዋል። ለዚህም ስኬት ሚኒስቴሩ የበኩሉን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

ለ15 ዓመታት ይህን ኢኒሼቲቭ እውን እንዲሆን ሲሰሩ የነበሩት ጥበቡ አሰፋ በበኩላቸው አፍሪካ ከአሜሪካ ጋር ያላት ግኙኝነት ከልመና ነፃ የሆነ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ታስቦ የተጀመረ በመሆኑ ፋይዳው የጎላ ነው ብለዋል።

በመድረኩ በቡና ልማት ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ኤጀንሲዎች ከብለስ ኮፊ አፍሪካ ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን የውል ስምምነት የፈረሙ ሲሆን፤ በአገሪቱ የሚገኙ 99 ሺሕ የኅብረት ሥራ ኤጀንሲዎች በኢኒሼቲቩ ተጠቃሚ እንደሚሆኑም የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ዑስማን ሱሩር ገልፀዋል።

ለበለጠ መረጃ፤

https://waltainfo.com/am/ የአፍሪካ-አሜሪካ-ትብብር/

## በኢትዮጵያ የአሜሪካ ንግድ ምክር ቤት የኢትዮጵያና የአሜሪካ የንግድ ግንኙነት ያሳሰበኛል አለ



በኢትዮጵያ የአሜሪካ ንግድ ምክር ቤት የኢትዮጵያና የአሜሪካ የንግድ ግንኙነት እንደሚያሳስበው አስታወቀ፡፡ አፍሪካ ግሮውዝ ኤንድ ኦፖርቹኒቲ አክት (አጎዋ) በመባል የሚታወቀውን የንግድ ተጠቃሚነትን ዕድል፣ ከኢትዮጵያ እንዳታጣ ሁለቱ መንግሥታት በአጽንኦት እንዲያስቡበት ጠይቋል፡፡

የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት አቶ ኤርሚያስ እሸቱ፣ የፌርፋክስ አፍሪካ ፈንድ መሥራች አቶ ዘመዴነህ ንጋቱና የሶል ሬበልስ ጫማ አምራች መሥራችና ባለቤት ወ/ሮ ቤተልሔም ጥላሁን መስከረም 20 ቀን 2013 ዓ.ም. ጉዳዩን በተመለከተ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከታሪፍና ከኮታ ነፃ የሆነውንና በኢትዮጵያ የሚመረቱ ምርቶችን ወደ አሜሪካ ገበያ ያለ ታሪፍና ኮታ እንድታስገባ፣ አጎዋ ለተባለው ተጠቃሚነት አባል የሆነችው ከ20 ዓመታት በፊት ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ይህንን ተጠቃሚነት አገሪቱ እንድታጣ ለማድረግ፣ መቀመጫውን በአሜሪካና በሌሎች ምዕራባውያን አገሮች ያደረገው በአሸባሪነት የተሰየመው የሕወሓት ደጋፊ ቡድን ቅስቀሳ ማድረግ የጀመረው ከወራት በፊት ነበር፡፡

በአሁኑ ወቅት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል እየተካሄደ ባለው ጦርነት ተፈጸመ ባለው ሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት፣ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን በኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብ እንዲጣል ትዕዛዝ ያስተላለፉት ከሁለት ሳምንታት በፊት እንደነበር ይታወሳል፡፡

በዚህም ሳቢያ በሁለቱ አገሮች መካከል እየተካረረ የመጣው ግንኙነት ሥጋት የፈጠረባቸው በኢትዮጵያ የአሜሪካ ንግድ ምክር ቤት አባላት፣ በኢትዮጵያ አሁን እየታየ ካለው ሁኔታ በመነሳት የሁለቱ አገሮች የንግድ ትስስር እየላላ ከመጣ ኢትዮጵያ ውስጥ ብቅ ብቅ እያሉ ያሉ የንግድ ተዋንያንን ሊያከስም እንደሚችል ፕሬዘዳንቱ አስረድተዋል፡፡

አጎዋን በመጠቀም ወደ አሜሪካ ገበያ የሚልኩ ግዙፍ ኩባንዎች መኖራቸውን የገለጹት አቶ ኤርሚያስ፣ በዕድሉ መነሳት ምክንያት ኩባንያዎቹ ከአገር ወጡ ማለት በፋብሪካዎች ተቀጥረው ሕይወታቸውን በሚመሩ ሴቶችና ወጣቶች ላይ መፍረድ ይሆናል ብለዋል፡፡

የሶል ሪበልስ ጫማ አምራች ባለቤት ወ/ሮ ቤተልሔም፣ በዘርፉ በቆዩባቸው ጊዜያት አሁን ለደረሱበት ደረጃ አጎዋ ትልቁን አበርክቶ እንደሚይዝ ገልጸዋል፡፡

በተለይም ከ320 በላይ ሠራተኞችን ቀጥረው በሚያሠሩበት ድርጅታቸው፣ በአጎዋ አማካይነት 75 በመቶ የሚሆነውን ምርታቸውን ወደ አሜሪካ ገበያ መላክ እንደቻሉ ገልጸዋል፡፡

‹‹በመሆኑም ይህን ዕድል ማጣት ዋጋ ያስከፍለናል፤›› ያሉት ወ/ሮ ቤተልሔም፣ በተቻለ መጠን ከአሁኑ ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል አቶ ዘመዴነህ በዚህ ዕድል 38 የአፍሪካ አገሮችን ተጠቃሚ እያደረገ የሚገኘው የአጎዋ ተጠቃሚነት ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ሰፋ ያለ ምርት ያለ ቀረጥ እንድትልክ የሚፈቅድላት ቢሆንም፣ እስካሁን ወደ አሜሪካ ገበያ የላከችው በጣም ውስን እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ መጥተው እያመረቱ ያሉ በርካታ ግዙፍ ኩባንያዎችና ገና ለመምጣት በዕቅድ ላይ ያሉ ባለሀብቶች ዋነኛ ምክንያታቸው ለኢትዮጵያ የተሰጠው ከቀረጥ ነፃ ዕድል ግምት ውስጥ በማስገባት በመሆኑ፣ ተጠቃሚነቱን ላለማጣት በሁለቱም ወገኖች የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጥረት ሊያደርጉ እንደሚገባ አቶ ዘመዴነህ አሳስበዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በአጎዋ ዕድል ተጠቃሚ የሆኑና በኢትዮጵያ እያመረቱ ወደ አሜሪካ የሚልኩ ኩባንያዎች ውስጥ፣ 230,000 ኢትዮጵያውያን ተቀጥረው እንደሚሠሩ ተጠቁሟል፡፡

እንደ አቶ ዘመዴነህ ገለጻ የአጎዋን ዕድል ኢትዮጵያ ከተነጠቀች፣ ቢያንስ አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተጎጂ ይሆናሉ፡፡

በመሆኑም የአሜሪካ መንግሥት እ.ኤ.አ ኅዳር 1 ቀን 2021 ኢትዮጵያ ትቆይ አትቆይ ብሎ ከመወሰኑ በፊት፣ መንግሥታቱ መፍትሔ ሊፈልጉ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethiopianreporter.com/article/23351

## በንግድ ዘርፉ ተዋናዮች ላይ በተወሰደ ዕርምጃ መሻሻል የጀመረው የዋጋ ንረት



ከወቅታዊ የዋጋ ንረቱ ጋር በተያያዘ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል እየተወሰዱ ያሉ ዕርምጃዎች ለውጥ እየታየባቸው መሆኑ ተጠቆመ፡፡ እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ለመከላከል ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ወደ ተግባር መግባቱን የሚያመለክተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መረጃ፣ በፌዴራል ደረጃ የተቋቋመው ዋጋ ማረጋጊያ በሚመለከት ሰሞኑን በኦሮሚያ፣ ደቡብ ሲዳማና አማራ ክልሎች፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ ዙሪያ ግብረ ኃይሉ በመዘዋወር በንግዱ ዘርፍ ያገኛቸውን ችግሮችና አሁናዊ ሁኔታዎች ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ሪፖርት አቅርበዋል፡፡ በዚህም መሠረት ምርት መደበቅ፣ ሱቅ መዝጋት፣ የሽያጭ ደረሰኝ ያለመስጠትና ቢሰጡም የሚሸጡበት ዋጋና ደረሰኝ ላይ የሚጻፈው ዋጋ መለያየት፣ የዋጋ ዝርዝር ያለመለጠፍና የደላሎች በሁሉም የግብይት ቦታዎች መግባት የተስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ሆነው መገኘታቸውን በቀረበው ሪፖርት ላይ ተጠቅሷል፡፡ አቶ መላኩም፣ በአሁኑ ወቅት መንግሥት የህልውና ዘመቻ እያካሄደ ባለበት ወቅት፣ እንደዚህ ያለ የኢኮኖሚ አሻጥር መፍጠር በሸማቹ ማኅበረሰብ ላይ ኢኮኖሚያዊ ጫና ለመፍጠር የሚደረጉ እኩይ ተግራት ተቀባይነት እንደማይኖራቸው ማስታወቃቸውን ከሚኒስቴሩ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ለኑሮ ውድነቱ መባባስ እንደ ትልቅ ተግዳሮች ከሚጠቀሱት ጉዳዮች ውስጥ፣ በግብይት ሒደቱ የሕገወጥ ደላሎች ጣልቃ ገብነት አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፣ እነዚህና መሰል የሥርዓተ አልበኝነት ችግሮችን ከሥሩ ለማድረቅ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከፌዴራል ፖሊስና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራና ይህም ውጤት እያመጣ ስለመሆኑ አስታውቋል፡፡

እስካሁን በግብረ ኃይሉ በተወሰዱ ዕርምጃዎች ለውጦች ታይተዋል ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ፣ በኦሮሚያ ክልል ከኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ እየተወሰደ ባለው ዕርምጃ የዋጋ መረጋጋትና መቀነስ የታየ ሲሆን፣ አንዳንድ ምርቶች ላይ ከ200 እስከ 1,500 ብር ቅናሽ መታየቱ ተጠቁሟል፡፡

በከተሞች መጋዘኖች እየተፈተሸ ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴ የመቆጣጠር ሥራዎችና የንግድ አሻጥሮችን የመለየት ሥራ መከናወኑንም በግብረ ኃይሉ እንቅስቃሴ የተመለከቱ መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ በሕገወጥ እንቅስቃሴ ተሰማርተዋል የተባሉ ነጋዴዎች ላይ ዕርምጃ እየተወሰደ ሲሆን፣ ከሰሞኑም ከ50 ሺሕ ብር እስከ ሦስት ወራት በሚደርስ እስራት የተቀጡ ነጋዴዎች መኖራቸውን የግብረ ኃይል ኮሚቴው ሪፖርት አመላክቷል ተብሏል፡፡ በዚህም ምክንያት በተወሰኑ ከተሞች በአንዳንድ ሸቀጣ ሸቀጦች ላይ እስከ 1,500 ብር ድረስ የዋጋ ቅናሽ መታየቱን የሚያትተው ይኼው ሪፖርት የሌሊት ድብቅ ንግድ መበራከት፣ የገበያ ትስስር ችግርና የምርት እጥረት ደግሞ አሁንም በንግዱ ሥርዓት ላይ ማነቆ ሆነው እንደሚታዩ ተጠቅሷል፡፡

በኦሮሚያ በተወሰደ ዕርምጃ ወደ 135 ሺሕ የንግድ ተቋማት ተፈትሸው፣ ከ10 ሺሕ በላይ በሚሆኑት ላይ የገንዘብና የእስራት ቅጣትን ጨምሮ የተለያዩ ሕጋዊ ዕርምጃዎች መወሰዳቸው ታውቋል፡፡ ዕርምጃው ሥርዓት አልበኝነትን መግታት፣ የኑሮ ውድነቱን ማረጋጋትና የዋጋ መቀነስ እንዲመጣ ጉልህ ሚና እያበረከተ መሆኑም እየተገለጸ ነው፡፡ በአዲስ አበባ የኢኮኖሚ አሻጥር በመፍጠራቸው 1,967 ንግድ ድርጅቶች ላይ ዕርምጃ መውሰዱን የከተማዋ ንግድ ቢሮ አስታውቋል፡፡ እንዲሁም የዋጋ ንረቱን ከመቆጣጠር ባለፈ በተወሰነ መልኩም ቢሆን አንዳንድ ምርቶች ላይ የዋጋ ቅናሽ መታየቱንና የበዓል ገበያው የተረጋጋ ሆኖ እንዲያልፍ የቁጥጥር ግብረ ኃይሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደነበረው ቢሮው አስታውቋል፡፡

በአዲስ አበባ ከ31,278 በላይ የንግድ ተቋማት መጎብኘታቸው የተገለጸ ሲሆን፣ በ1,967 ንግድ ድርጅቶች ላይ ሕጋዊና አስተዳደራዊ ዕርምጃዎች መወሰዱን ገልጿል፡፡ በቀጣይም በኢኮኖሚ አሻጥር ላይ በሚሳተፉ ሕገወጥ ነጋዴዎች ላይ የሚወሰደው ዕርምጃ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ደግሞ የከተማ አስተዳደሩ ፕሬስ ሴክሬተሪያት ጽሕፈት ቤት መረጃ አመልክቷል፡፡

በሚኒስቴሩ የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር ወ/ሮ አበባ ታመነ ሰሞኑን በሰጡት መግለጫ ደግሞ፣ መንግሥት የኢኮኖሚ አሻጥርን ለመከላከል ያቋቋመው ግብረ ኃይል በሕገወጦች ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊ ዕርምጃ በመጠቀም፣ የግብረ ኃይሉ ባደረገው መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ በሕገወጥ መንገድ ሲንቀሳቀስ የነበረ 250 ኩንታል ሰሊጥ፣ እንዲሁም በሐረሪ ክልል አራት መኪና ሸንኩርት አየር በአየር ሲሸጥ በቁጥጥር ሥር ማዋሉን ተናግረዋል፡፡ በደቡብ ክልል በሃላባ ዞን ስምንት ሕገወጥ ደላሎች ላይ የእስራት ዕርምጃ መውሰዱንና በሕገወጥ መንገድ የተከማቸና ከፍተኛ ግምት ያለው ብረት መያዝም ከዚሁ ግብረ ኃይል እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ መሆኑ ተገልጿል፡፡

እንዲህ ያሉ ዕርምጃዎች እየተወሰዱ ቢሆንም፣ አሁንም ገበያው በታሰበው ልክ እየተረጋጋ ያለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ እንደ ወ/ሮ አበባ ገለጻም፣ አስተማሪ ዕርምጃዎች ይወሰዱ እንጂ አሁንም በቀጣይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው መሠራት የሚገባቸው ጉዳዮች መኖራቸውን ተናግረዋል፡፡ በተለይ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ እየተፈጠረ ላለው የኢኮኖሚ አሻጥር የአንባሳውን ድርሻ የሚይዘው በግብይት ሒደቱ ላይ ምንም እሴት የማይጨምሩ የሕገወጥ ደላሎች ጣልቃ ገብነት መሆኑን አመልክተዋል፡፡ እነዚህን ሕገወጥ አካላት አደብ ለማስያዝ በደቡብ ክልል በሃላባ ዞን የታየው በጎ ጅማሮ በሌሎች ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮችም ሊተገበር እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከንግድ ሥርዓቱ ጋር በተያያዘ ‹‹እየወሰድኳቸው ናቸው›› ካላቸው ዕርጃዎች ባሻገር፣ ሕወሓት በሥልጣን በቆየባቸው ዓመታት በርካታ አሻጥሮች እንደተሠሩ በመግለጽ፣ እነዚህን አሻጥሮች ለመበጣጠስ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ ማመልከቱ አይዘነጋም፡፡ በተለይ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ይህንን፣ ‹‹አሸባሪውና ዘራፊው ቡድን ሥልጣን ላይ በቆየባቸው 27 ዓመታት በርካታ የኢኮኖሚ አሻጥሮችን ሲሠራ ነበር፤›› ብለዋል፡፡

በነፃ ኢኮኖሚ ሥርዓት ሽፋን አንድን አካል ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርግ ፖሊሲ ማውጣት፣ የመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካን ብቻ ተጠቃሚ ለማድረግ፣ ተጨማሪ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች እንዳይገነቡ የሚያግድ ፖሊሲ እስከ ማውጣት የተደረሰበት እንደሆነ አቶ መላኩ ጠቁመዋል፡፡ ለኮንስትራክሽን የሚውሉ ግብዓቶችን በውስንና ለአሸባሪ ቡድን ታማኝ በሆኑ አካላት ብቻ ከውጭ እንዲመጡ መፍቀድ፣ በኢንቨስትመንት ሽፋን ሰፋፊ መሬቶችን በመያዝ ከባንኮች የብድር አገልግሎት መጠየቅና ብድሩን በተገቢው ዲሲፕሊን አለመመለስ ከተሠሩ አሻጥሮች ውስጥ ተጠቃሾች መሆናቸውንም መግለጻቸው ይታወሳል፡፡

ይህንን የኢኮኖሚ አሻጥር የተረዳው የለውጡ ኃይል፣ ከለውጡ እዚህን ችግሮች ለመቅረፍ እንቅስቃሴ እያደረገ ባለበት ወቅት ይህ ጽንፈኛ በአገሪቱ ላይ በከፈተው ጦርነት የተፈለገው ውጤት እንዳልመጣ ያመለከቱት አቶ መላኩ፣ በአሁኑ ወቅት ይህንን የኢኮኖሚ አሻጥር ለመቀልበስና በአገሪቱ ላይ አላስፈላጊ ዋጋ ጭማሪ እንዳይፈጠር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለሀብቶች ጋር ስምምነት ላይ ተደርሷል ብለዋል፡፡ አሁን ያለንበት ወቅት አስከፊና ፈተና የበዛበት በመሆኑ በተለይ የአገራችን ባለሀብቶች ትርፍ ኅዳጋቸውን ከማሰብ ይልቅ አገርን ወደ ማዳን አንድምታ መሸጋገር እንደሚገባቸውም ማሳሰባቸው አይዘነጋም፡፡

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርም እንዲህ ያሉ አሻጥሮችን ለመከላከል ኅብረተሰቡ መተባበር እንዳለበትና ጥቆማ መስጠቱንም እንዳያቆም እያሳሰበ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethiopianreporter.com/article/23268

## ባህር ትራንስፖርት 10 ሚሊዮን ቶን ገቢና ወጪ ጭነቶችን ለማጓጓዝ እየሠራሁ ነው አለ



የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በተያዘው የበጀት ዓመት፣ ከአሥር ሚሊዮን ቶን በላይ ገቢና ወጪ ጭነቶችን ለማስተናገድ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሮባ መገርሳ ለሪፖርተር እንዳስረዱት፣ የ2014 ዓ.ም. በጀት ዕቅድ ተዘጋጅቶና በሚመለከታቸው ሁሉም አካላት ውይይት ተደርጎበት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ፀድቆ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፣ ድርጅቱ በተያዘው የበጀት ዓመት ከአሥር ሚሊዮን ቶን በላይ የገቢ ወጪ ጭነቶችን ለማስተናገድ ዕቅድ ይዟል፡፡ ከወጪና ገቢ ጭነቶች ውስጥ ከፍተኛ የሆነውን ድርሻ የሚይዘው የአፈር ማዳበሪያ ነው፡፡ ድርጅቱ ባለፈው የበጀት ዓመት ያጓጓዘው አጠቃላይ ገቢና ወጪ ጭነት 8.3 ሚሊዮን ቶን እንደነበር አቶ ሮባ አስታውሰዋል፡፡

በተያዘው ዓመት የሚጓጓዘው የአፈር ማዳበሪያ ሁለት ሚሊዮን ቶን እንደሚሆን ይጠበቃል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ ይህ ማዳበሪያ በተወሰነለት ጊዜ ግዥው ከተጠናቀቀ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት መርከቦችን አሰማርቶ ማጓጓዝ እንደሚጀምርና ለአርሶ አደሩም በጊዜው እንዲደርስ አስፈላጊው ዝግጅት እንደተደረገ አስታውቀዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ የ240 ከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች ግዥ እንደሚፈጸም፣ ለ38 ተሽከርካሪዎች ግዥ ትዕዛዝ እንደተላለፈ አቶ ሮባ ተናግረዋል፡፡ ባለፈው የበጀት ዓመት ድርጅቱ ከ11 ሚሊዮን ዶላር በላይ በማውጣት 150 የከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎችን መግዛቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ድርጅቱ ባቡርም የሚጠቀምበት አማራጭ እንዳለ አስገንዝበዋል፡፡ አልፎ አልፎ ከሚያጋጥመው የፀጥታ ችግር በስተቀር ድርጅቱ በጥሩ ሁኔታ እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

«በጁቡቲ ወደብ በኩልም አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ምክክሮችን አድርገናል፤» ያሉት አቶ ሮባ፣ በወደቡ በኩል በሥጋትነት ሊነሳ የሚችለው ጉዳይ ባሳለፍነው ዓመት አጋጥሞ በርብርብ ለማቃለል የተሞከረው ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተያያዘው ችግር እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ባልተለመደ ሁኔታ ጂቡቲ ዝናባማ አገር እየሆነ መጥቷል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ በወደቡ ያሉት አገልግሎቶች ለዝናባማ የአየር ፀባይ የተዘጋጁ ስላልሆኑ፣ የወደብ ማሽነሪዎች በተደጋጋሚ ጊዜ እንደሚበላሹና ተጨማሪ የወደብ ማሽነሪዎች እንዲገዙ ጥያቄ መቅረቡን ጠቁመዋል፡፡

ሌሎች የወደብ አማራጮችን ከመጠቀም ወደኋላ እንደማይባልና ወደ በርበራ መሄድም አስፈላጊ ከሆነ ዝግጅቶች ተደርገው የሚኬድ ይሆናል ብለዋል፡፡

ድርጅቱ በተያዘው የበጀት ዓመት ትኩረት ሰጥቶ ከሚሠራባቸው ጉዳዮች የመርከብ ዴሜሬጅን መቀነስ እንደሆነ ገልጸው፣ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰትን ተከትሎ የመርከብ ማጓጓዣ ዋጋ ከሚታሰበው በላይ በመናሩ፣ የዓለምን የመርከብ ሥምሪት ቁጥጥር በአሜሪካና በቻይና ላይ በመውደቁ ያለውን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ወደብ የሚደርሱ ጭነቶችን በወቅቱ ማንሳት ወሳኝ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡

እንደ አቶ ሮባ ገለጻ፣ የመርከብ የጭነት ዋጋ ከዓመት በፊት ከነበረው አሥር እጥፍ ነው ያደገው፡፡ ይህም ታይቶ የማይታወቅ ነው ብለዋል፡፡ በወረርሽኙ ምክንያት በነበረው የእንቅስቃሴ ገደብ ምክንያት ሳይንቀሳቀሱ የቆዩ ጭነቶች በመኖራቸው ለማንሳት በሚደረገው ሒደት ወረፋዎች መብዛታቸውን፣ ባልተለመደ ሁኔታ ቻይና ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ መርከቦች ወረፋ እየጠበቁ መሆናቸው፣ በሁለትና በሦስት ቀናት መርከብ የሚስተናገድበት አሠራር እስከ 23 ቀናት እየፈጀ መሆኑ፣ በተለይ በቻይና አሁን የሞንሱን አየር ፀባይ ሌላው ችግር መሆኑን አውስተዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች የኮንቴይነር አቅርቦትን እንዳስተጓጎሉ የጠቀሱት አቶ ሮባ፣ ከዚህ ሁሉ በላይ የዕቃዎች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እንዳደገና የዩሪያ፣ የድንጋይ ከሰልና የብረት ምርቶች ዋጋ ከፍተኛ ጭማሪ ታይቶበታል ብለዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ መርከብ መቆም የለበትም በሚል ትኩረት ተሰጥቶ፣ አቅምን በዚህ ላይ አጎልብቶ እየተሠራ እንደሆነ ዋና ሥራ አስፈጻሚው አስታውቀዋል፡፡

ከወደብ አገልግሎት አሰጣጥ አኳያ በሞጆ ደረቅ ወደብ በጥሩ ሁኔታ አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ ተመቻችቷል የተባለ ሲሆን፣ ጭነት ወደብ ላይ እንዳይቆይና በባቡር የሚመጣ ጭነት እንዲሁ በቶሎ እንዲራገፍ፣ በተለይም የአፈር ማዳበሪያን መቀበል የሚያስችሉ ሁለት መጋዘኖች ተሠርተው መጠናቀቃቸው ተመልክቷል፡፡

ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ የወጣበትና 34 ሔክታር መሬት ላይ ያረፈው ዘመናዊው የድሬደዋ ደረቅ ወደብ፣ በተያዘው የበጀት ዓመት ወደ ሥራ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ በተያዘው የበጀት ዓመት ትልቅ ተግዳሮት ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው የመርከብ የማጓጓዣ ዋጋ ንረትና የኮንቴይነር እጥረት እንደሆነ ያስታወቁት አቶ ሮባ፣ በቅርቡ ከተገዙት አምስት ሺሕ ኮንቴይነሮች በተጨማሪ በቅርቡ አምስት ሺሕ ኮንቴይነሮች እንደሚገዙ አስታውቀዋል፡፡

የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ሌላው ችግር ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች ተጠቃሹ እንደሆነ ያወሱት አቶ ሮባ፣ የጂቡቲ ወደብ ዕቃዎችን የማስተናገድ አቅም በጭነት መጠኑ ልክ አለማደጉ ሌላው ችግር እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ በወደቡ የሚስተናገዱ ጭነቶች መጠን በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ ቢሆንም፣ ማሽነሪዎች ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ በብልሽት ምክንያት የሚቆሙበት ሁኔታ እንደሚስተዋል ገልጸው፣ የማሽነሪና የአየር ሁኔታው ተጨማምሮ ስለማይቻል ይህ ጉዳይ ራሱን የቻለ ፈተና እንደሚሆን አስታውቀዋል፡፡

የአገሪቱ የግዥ ሥርዓት ችግር ሌላው ያልተፈታ መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነ የጠቀሱት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ ግዥ በተፈለገው ጊዜ ስለማይካሄድ የመርከብ ጭነቶችን እንቅስቃሴ እንደሚያዛባና በተለይ የስንዴና የማዳበሪያ ግዥ ሒደት ትንሽ አስቸጋሪ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ የጭነት ተሽከርካሪዎች ቁጥር እጥረት እንደቀደሙት ጊዜያት ሁሉ የተለመደ መሆኑን ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገልጸው፣ በአብዛኛው ወደ ወደብ የሚሄዱ ተሽከርካሪዎች የዕርዳታ እህል ጭነው አልተመለሱም እየተባለ ስለሆነ የዕርዳታ ፍላጎቱም እያደገ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ ተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን ማሰማራት አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ያለው ብቸኛ አማራጭ ተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን መግዛት እንደሆነ ታሳቢ ተደርጎ፣ መንግሥት 3,200 ያህል የጭነት ተሽከርካሪዎችን በተለያዩ ተቋማት አማካይነት እንዲገዙ ትዕዛዝ ሰጥቶ እየተሄደበት እንደሆነ አቶ ሮባ አስረድተዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethiopianreporter.com/article/23290

## ብሔራዊ ባንክ የግምጃ ቤት ሰነድ አሠራር የሚለውጥ መመርያ አወጣ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በባንኮች ላይ ተጨማሪ ጫና ይፈጥራል የተባለውንና ከግምጃ ቤት ሰነድ ጋር በተያያዘ፣ ተጠቃሚ ይሆኑበት የነበረውን አሠራር የሚቀይር መመርያ ማውጣቱ ተሰማ፡፡

ሪፖርተር ባገኘው መረጃ መሠረት ከዚህ ቀደም ባንኮች በግምጃ ቤት ጨረታ የሚሳተፉት የግምጃ ቤት ሰነድን ለ28 ቀናት፣ ለ60 ቀናት፣ ወይም ለ90 ቀናት ሲሆን፣ ለ365 ቀናት የሚገዙ ባንኮች አሉ፡፡ ጨረታውን ሲገዙም በተጫረቱበት ዋጋ ወለድ የሚታሰብላቸው ሲሆን፣ በሰጡት የወለድ መጠን ልክ ገንዘቡን ያገኙታል፡፡

በመሀል ላይ ግን ባንኮች የገንዘብ እጥረት ሲገጥማቸው፣ ገንዘቡን ለሚፈልጉት ዓላማ ለማዋል ብሔራዊ ባንክን ጠይቀው መልሰው የመውሰድ ዕድል ነበራቸው፡፡ አሁን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመርያ ግን ይህንን ዓይነቱ አሠራር ይቋረጣል፡፡ እስካሁን በነበረው አሠራር ለምሳሌ አንድ ባንክ ለ60 ቀናት ሰነዱን ከገዛ በኋላ፣ ባንኩ ገንዘቡን ቢፈልግ እስከ አርባኛው ቀን ድረስ ከሰነዱ ይገኝ የነበረውን ወለድ በማስቀረት ገንዘቡ ይመለስለትና ችግሩን ይወጣበት ነበር፡፡

አሁን ግን ሰነዱ ከተገዛ በኋላ እንደ ቀድሞ ገንዘቡን ልጠቀምበት ብሎ ባንኩ ቢያመለክት፣ በመመርያው መሠረት ያንን ገንዘብ ማግኘት አይችልም፡፡ አሁን በወጣው መመርያ መሠረት የግምጃ ቤት ሰነድ የተገዛበትን ገንዘብ በመሀል ላይ እንደ በፊቱ መውሰድ ስለማይቻል፣ ባንኮች የግድ ከብሔራዊ ባንክ በ16 በመቶ ወለድ እንዲበደሩ የሚያደርጋቸው መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ባንኮች የግምጃ ቤት ሰነዱን ወለድ በማስቀረት ዋናውን ገንዘብ መልሰው ማግኘታቸው የሚጠቅመው፣ ከብሔራዊ ባንክ በ13 በመቶ ወለድ ከመበደር የተሻለ ጥቅም ስለሚያገኙበት ነው፡፡ አሁን ደግሞ ብሔራዊ ባንክ የማበደሪያ መጠኑን 16 በመቶ በማድረሱ በ16 በመቶ ወለድ ተበድረው ጊዜያዊ ችግራቸውን ለመቅረፍ ቢሞክሩ አዋጪ ስለማይሆንላቸው፣ በባንኮቹ ላይ ጫና ይፈጥራል እየተባለ ነው፡፡

በጉዳዩ ላይ ሪፖርተር ያነጋገራቸው የባንክ ባለሙያዎች እንደገለጹት፣ ከአምስት ሺሕ ብር ጀምሮ በግምጃ ቤት ሰነድ ጨረታ ላይ ማንም ሰው መሳተፍ ይችላል፡፡ እንዲህ ባለው ጨረታ እስካሁን በይበልጥ እየተሳተፉ ያሉት ባንኮች ነበሩ፡፡

በአዲሱ አሠራር ገንዘብ በቀላሉ ማግኘት እንደሚቻል፣ ባለፈው ሳምንት ብሔራዊ ባንክ ባስተላለፈው ሰርኩላር ማቆሙን፣ ከዚህ በኋላ በአዲሱ መመርያ መሠረት ባንኮቹ ከብሔራዊ ባንክ ገንዘብ ቢፈልጉ በ16 በመቶ ወለድ መሠረት መስተናገድ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡

የብሔራዊ ባንክ መመርያ ባንኮች ለግምጃ ቤት ሰነድ በመጫረታቸው ያገኙት የነበረውን ጥቅም የሚያሳጣቸው በመሆኑ፣ ከዚህ በኋላ በጨረታ ለመሳተፍ የነበራቸውን ተነሳሽነት ሊቀንስ እንደሚችልና ዕርምጃው ተጨማሪ ጫና የሚፈጥር ነው የሚሉት የባንክ ባለሙያዎች፣ የብሔራዊ ባንክ ሰሞናዊ አካሄድ ግራ እንዳጋባቸው ሳይጠቅሱ አላለፉም፡፡ በተለይ ነገሩን የበለጠ አሳሳቢ ያደርገዋል ያሉት ብሔራዊ ባንክ ተከታታይ መመርያዎች ያወጣበት ጊዜ ነው ይላሉ፡፡

ይህንንም ሲያብራሩ ወቅቱ የግብር መክፈያ ጊዜ በመሆኑ ባንኮቹ ገንዘብ የሚያገኙበት መንገድ በተዘጋ ቁጥር ለባንኮቹ ብቻ ሳይሆን፣ በደንበኞቻቸው ላይም ጫና የሚፈጥር በመሆኑ ነው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ከአንድ ሳምንት በፊት በወጡ ተከታታይ መመርያዎች፣ ባንኮች በብሔራዊ ባንክ ያስቀምጡ የነበረውን አምስት በመቶ መጠባበቂያ ገንዘብ ወደ አሥር በመቶ ማሳደግ እንዳለባቸው መደንገጉ ይታወሳል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ባንኮች ከእያንዳንዱ ከሚሰጡት ብድር አንድ በመቶ ለቦንድ ግዥ ማዋል እንደሚኖርባቸውም በቅርቡ በወጣ መመርያ የተደነገገ ሲሆን፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎችም ከሚያገኙት ዓመታዊ ትርፍ 15 በመቶ ለቦንድ ግዥ ማዋል አለባቸው ተብሏል፡፡ እንዲህ ያሉ አዳዲስ መመርያዎች በባንኮች ላይ ጫና የሚያሳድሩ መሆናቸውን፣ አሁን ደግሞ ለግምጃ ቤት ሰነድ ላይ የተጫረቱበትን ገንዘብ አስቸኳይ ጉዳይ ሲገጥማቸው መልሰው በመውሰድ ይጠቀሙበት የነበረውን አሠራር ሲለወጥ ጫናውን የበለጠ ያደርግባቸዋል ተብሏል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethiopianreporter.com/article/23228

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሰባት ኩባንያዎች የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ምርት ፈቃድ እንዲሰጥ ተጠየቀ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከ47 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ለሚያስገኙ ሰባት ኩባንያዎች፣ የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ምረት ፈቃድ እንዲሰጥ ተጠየቀ።

ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበው የውሳኔ ሐሳብ ለመጀመርያ ጊዜ የከፍተኛ ደረጃ የብሮሚንና የክሎሪን ማዕድን ምርት ፈቃድ እንዲሰጥ የተጠየቀበት እንደሆነ የሪፖርተር ምንጮች ገልጸዋል።

በጥቅሉ ወደ ምርት ለመግባት የከፍተኛ ደረጃ የምርት ፈቃድ እንዲሰጣቸው የተጠየቀው ለሰባት ኩባንያዎች ሲሆን፣ የኩባንያዎቹ አጠቃላይ ካፒታል 18.58 ቢሊዮን ብር እንደሆነ ምንጮች ገልጸዋል።

ከማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ወስደው አዋጭ የወርቅ ምርመራ ሲሠሩ የነበሩ አራት የወርቅ ማዕድን ኩባንያዎች፣ ሁለት የእምነበረድ፣ ከጨዋማ ሐይቅ የብሮሚንና የክሎሪን ማዕድን ፍለጋ በማከናወን ላይ የነበረ አንድ ኩባንያ ናቸው።

የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር የሕግ፣ የቴክኒክና የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ቡድን በማቋቋም የኩባንያዎቹን ማመልከቻ ገምግሟል።

በዚህም የኩባንያዎቹን የምርት ቦታና ዓይነት፣ መነሻ ካፒታላቸውን፣ የፕሮጀክቶቹ አዋጭነትና ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ እንደ ገመገመ፣ እንዲሁም የባለሙያዎቹ አስተያየትን በማከል የውል ስምምነት ድርድር ከኩባንያዎቹ ጋር አድርጎ የመጨረሻ የውሳኔ ሐሳቡን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቅረቡን ከምንጮች የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ኩባንያዎቹ ከ47 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ እንደሚያስገኙ jአዋጭነት ጥናት መገመቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከፍተኛ የወርቅ ማዕድን የማምረት ፈቃድ የጠየቁት አራት ኩባንያዎች ለመሰማራት የጠየቁበት የወርቅ ክምችት የሚገኘው በጋምቤላ ክልል ሲሆን፣ ብሮንዝና ክሎሪን ለማምረት ከፍተኛ የማዕድን ማምርት ፈቃድ የጠየቀው ኩባንያ ደግሞ በአፋር ክልል የሚገኘውን ክምችት ለማምረት መጠየቁን መረጃው ያመለክታል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethiopianreporter.com/article/23229

## የንግዱ ማህበረሰብ እና አምራቾች ባለሃብቶች ሃገርን የማሻገር ትልቅ ሃላፊነት ያለባቸው መሆኑ ተገለፀ

መንግስት በአሁኑ ወቅት የህልውና ዘመቻ እያደረገ ባለበት ወቅት አንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች በሚፈጥሩት አላስፈላጊ የዋጋ ጭማሪ በተለይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የህብረሰብ ክፍሎች ላይ አላስፈላጊ የኢኮኖሚ ጫና እየተፈጠረ እንደሚገኝ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኮሙኑኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ አበባ ታመነ ገልጸዋል፡፡

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳት ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ እንዳለ የገለጹት ዳይሬክተሯ በዚህ በቅንጅት በተሰራው ስራ ለውጦች መታየታቸውን አመላክተዋል፡፡

ለዚህ ዓይነት እኩይ ተግባር የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው በግብይት ሂደቱ ላይ ምንም እሴት የማይጨምሩ የህገ-ወጥ ደላሎች እንቅስቃሴ እንደሆነና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሃገር አቀፍ ደረጃ ከተቋቋመው ግብረ-ሃይል ጋር በመሆን በነዚህ ህገ-ወጥ አካላት ላይ እርምጃ መወሰዱን ዳይሬክተሯ ገልጸዋል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሰራቸው የተለያዩ የቅንጅት ስራዎች ለውጦች ቢታዩም  ነገር ግን አሁንም በቀጣይ መሰራት የሚገባቸው በርካታ የቤት ስራዎች እንዳሉም ወ/ሮ አበባ አልሸሸጉም ፡፡

ኢትዮጵያ አዲስ መንግስት ለመመስረት መባቻ ላይ ባለችበት ወቅት ይህ በአሁኑ ወቅት በጁንታው ደጋፊዎች እና በግብረአበሮቹ እየተደረገ ያለው የኢኮኖሚ አሻጥር በምንም መልኩ ሃገርን ከማፈረስ ስለማይተናነስ ተቀባይነት እንደሌለው ወ/ሮ አበባ አስረድተዋል፡፡

ለቀጣይቷ ኢትዮጵያ የንግዱ ማህበረሰብ እና የአምራች ባለሃብቶች ሚና የጎላ ሚና እንዳለው የገለጹት ዳይሬክተሯ እነዚህ አካላትም ከትርፋቸው ይልቅ ሃገርን ወደ የማሻገር ዓላማ ብቻ ይዘው መንቀሳቀስ እንደሚገባቸው እና አዲስ ከሚመሰረተው መንግስት ጋር በመቆም ኢትዮጵያን ለማስቀጠል በጋራ እንዲሰሩ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.facebook.com/Ethiopia-Ministry-of-Trade-and-Industry-924090991312922/

## መቀመጫቸውን ጅቡቲ ያደረጉ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ ዘመናዊ ቄራ ለመገንባት ፍላጎት እንዳላቸው ገለጹ

ከተለያዩ የአፍሪካ አገራት የተውጣጡ መቀመጫቸውን ጅቡቲ ያደረጉ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ዘመናዊ ቄራ ለመገንባት ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል።

ባለሀብቶቹ በኢትዮጵያ ለሦስት ቀናት የኢንቨስትመንት ጉብኝትያደረጉ ሲሆን፥ ከከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ፣ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች እንዲሁም በአገሪቱ ካሉ የግሉ ዘርፍ ተወካዮች ጋር ተወያይተዋል።

በዚሁ ወቅት የልዑካን ቡድኑ ኃላፊ ሙስጠፋ ጃማ፥ አዲሱ የሚገነባው ዘመናዊ ቄራ ለእርድ የሚቀርቡ እንስሳቶችን ከማደለቢያ አንስቶ እስከ እርድ የሚኖረውን ሂደት ለአውሮፓ እና ሌሎች ደረጃቸውን ለጠበቁ ገበያዎች ሙሉ መረጃ ለማቅረብ የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል።

በተጨማሪም መርሃግብሩ ተግባራዊ ሲደረግ የመድኃኒቶችን እና የእንስሳት ጤና አያያዝን እንዲሁም የእርባታ ቴክኖሎጂን በማስተዋወቅ ለአርሶና አርብቶ አደሩ ሕይወት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋልም ነው ያሉት።

ከፍተኛ የመንግስት የስራ ሃላፊዎቹም፥ ባለሀብቶቹ መንግስት ቅድሚያ በሚሰጣቸው ዘርፎች በአንዱ ላይ ለመስራት ላሳዩት ጥልቅ ፍላጎት አመስግነዋል።

አያይዘውም እንደ እነዚህ ያሉ እቅዶች በመካከለኛው ምስራቅ ካሉ ባህላዊ ገቢያዎች ውጭ ያሉትን ገቢያዎችን እንደሚያሰፉም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በአህጉሪቱ በእንስሳት ሀብት ቀዳሚ አገር ብትሆንም እስካሁን ከዘርፉ የተገኘው ውጤት በጣም ደካማ በመሆኑ እነዚህን ሰፊ ዕድሎች ለመጠቀም ብዙ መስራት ይገባልም ነው ያሉት።

የስጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካው ሥራ ሲጀምር በቀን 600 በሬዎች ፣ 5 ሺህ በጎች እና ፍየሎች እንዲሁም 100 ግመሎችን በመጀመሪያው ዙር የማምረት አቅም ይኖረዋል ተብሏል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/በቀመጫቸውን-ጅቡቲ-ያደረጉ-ባለሃብቶች-በ/

## በአራተኛው የንግድ ትርኢት ላይ የ10 የተለያዩ አገራት ኩባንያዎች ይሳተፋሉ ተባለ




በግብርና፣ ምግብና መጠጥ ማቀነባበርና የፕላስቲክ ህትመት የንግድ ትርኢት የ10 የተለያዩ አገራት ኩባንያዎች እንደሚሳተፉ አዘጋጅጆቹ ተናገሩ።

አራተኛው የኢትዮጵያ የግብርና፣ ምግብና መጠጥ ማቀነባበርና የፕላስቲክ ህትመት የንግድ ትርኢት ከጥቅምት 4 እስከ 6 ቀን 2014 ዓ.ም በአዲስ አበባ ይካሄዳል።

የንግድ ትርኢቱ አዘጋጅ የሆኑት ፌር ትሬድ እና የፕራና ኤቨንት አዘጋጆች ከተለያዩ ተሳታፊ አገራት ኤምባሲ ተወካዮች ጋር በጋራ መግለጫ ሰጥተዋል።

የፕራና ኤቨንት ማኔጅንግ ዳይሬክተር አቶ ነብዩ ለማ፤ መንግስት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በከፍተኛ ወጪ መገንባቱን አንስተዋል።

የንግድ ትርኢትና ባዛር በኢንዱስትሪ ፓርክ የሚሰሩ ባለሃብቶች ዓለም የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ደረጃ እና ተሞክሮ ለመቅሰምና አላማቸውን ለማሳደግ ሚናው የጎላ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በንግድ ትርኢቱ በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያዩ ኩባንያዎች እንዲሁም ከቱርክ፣ ጀርመን፣ ኢጣሊያ፣ ፈረንሳይ፣ ህንድን ጨምሮ የ10 አገራት 40 ኩባንያዎችና ድርጅቶች ይሳተፋሉ ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

የፌር ትሬድ መስራች ማርቲን ማሬዝ፤ የንግድ ትርኢቱ የእውቀትና የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ጠቃሚ መሆኑን አብራርተዋል።

በዚህም የሀገር ውስጥ አምራቾች የእውቀት ሽግግር ለመፍጠርና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለማምረት እድል የሚፈጥር ነው ብለዋል።

በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክና ኢንዱስትሪ ልማት ማስተባበሪያ ዳይሬክተር አቶ አያልነህ አባዋ ኢትዮጵያ ለኢንዱስትሪ ልማት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እየሰራች መሆኑን ገልጸዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/ በአራተኛው-የኢትዮጵያ-የንግድ-ትርኢት-የ10/

## የኤክስፖ 2020 ዱባይ የኢትዮጵያ ፖቪሊዎን ለጉብኝት በይፋ ተከፈተ




በዱባይ በሚካሄደዉ ኤክስፖ 2020 በትላንትናው ዕለት የኢትዮጵያ ፓቪሊዮን ደማቅ የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ተካሂዷል።

በመክፈቻ ፕሮግራሙ ላይ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋና አረጋ እና የኤክስፖ 2020 ዱባይ የኢትዮጵያ ኮሚሽነር ጄኔራል፣ አምባሳደር እየሩሳሌም አምደማሪያም በዱባይ የኢፌዲሪ ቆንስል ጄኔራል እንዲሁም የንግድና ኢንዱስትሪ ኃላፊዎች በዱባይና ሰሜን ኤምሬቶች የተለያዩ አደረጃጀት ኃላፊዎችና የሃይማኖት አባቶች ተገኝተዋል።

ኤክስፖው በፈረንጆቹ  ከጥቅምት  1 ቀን 2021 እስከ መጋቢት 31 ቀን 2022 ድረስ የሚቆይ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

አምባሳደር ምስጋናዉ አረጋ ባደረጉት ንግግር፥ የዱባይ ኤክስፖ 2020 የአገራችንን ባህል፣ ታሪክ፣ የቢዝነስና ኢንቨስትመንት ዕድሎች እንዲሁም የቱሪስት መስህብን  ለማስተዋወቅና ገጽታችንን ለመገንባት ትልቅ ድርሻ እንዳለዉ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ እንደ አገር በፖቪሊዎን(Pavilion)  እንደምትካፈልና ተሳትፎዋን የተመለከተ ገለጻ አድርገው፥ ለዝግጅቱ መሳካት በዱባይና ሰሜን ኤምሬቶች የተለያዩ አደረጃጀት ኃላፊዎች፤ በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ለሚኖሩ ህፃናትና ለተባበሩት አረብ ኤምሬትስ መንግስት ምስጋና አቅርበዋል ።

በኤክስፖዉ የኢትዮጵያ ምርቶች የሚቀርቡበት፣የቱሪዝም ተደራሽነት የምናሳደግበት እንዲሁም የኢንቨስትመንት እድሎችን የምናስተዋወቅበት ትልቅ መድረክ  ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች መገኛ የሃይማኖቶች መቻቻል አብሮነት በሚገልጽና ኢትዮጵያ እንደ አገር ምድረ ቀደምት( Land of Origin and Opportunity) በሚሉ መሪ ቃሎች ዲያስፖራዉን ያሳተፉ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች በስድስት ወራት ዉስጥ እንደሚቀርቡና እንዲጎበኙ በድጋሚ ጥሪ  ተላልፏል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.facebook.com/Ethiopia-Ministry-of-Trade-and-Industry

# የቆዳ ሃብትን በአግባቡ ለመጠቀም በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን መቅረፍ ተገቢ ነው

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መገኛ መሆኗ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ብሄርብሄረሰቦችና ህዝቦችም የየራሳቸው እምነቶች እና ባህሎች ያሏቸው ሲሆን የሃይማኖት ስርዓታቸውን በተለያዩ መንገዶች ይከውናሉ፡፡ ሃይማኖታዊ ስርዓት ከሚከውንባቸው ተግባራት ውስጥ አንዱ የእርድ ስርዓት ሲሆን ሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት በሚከበሩ ሃይማታዊ በዓላት ጊዜ ለሚፈጸም እርድ የሚውል የእንስሳት ሀብት ባለቤት ናት፡፡ በየዓመት በዓላቱ ከሚፈጸሙ የእንስሳት እርዶች የሚገኘው ቆዳ ደግሞ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ምንጭ የሆነ ሌላኛው ጸጋ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ዓመት በዓል በመጣ ቁጥር በሚፈጸሙ በርካታ የእንስሳት እርድ የሚገኘውን ቆዳ ጥቅም ላይ በማዋል ልናገኝ የምንችለውን በሚሊዮኖች የሚቆጠር የውጪ ምንዛሬ እያጣነው እንገኛለን፡፡ በየዓመት በዓላቱ በሚፈጸም በርካታ የቁም እንስሳት እርድ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት የሚገኝ ሲሆን ይህ የቆዳ ምርት በተገኘው አቅርቦት መጠን ጥቅም ላይ ሲውል አይስተዋልም፡፡ ለዚህም በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ጉዳዮች ውስጥ ዘርፉን ለማሳደግ ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር አለመዘርጋቱ እና በአሁኑ ወቅት ያለው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት መሆኑን የቁም እንሰሳት ግብይትና ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ ዴስነት በላይ ይናገራሉ፡፡

በተደጋጋሚ ጊዜያት እንደተገለጸው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ወደፊት መጓዝ የሚችለው ከግብርና ዘርፍ ጋር ያለውን ሁሉ አቀፍ ትስስር ጠብቆ መጓዝ ሲችል ብቻ ነው፡፡ ይህ ማለት በሃገራችን የቆዳ ኢንዱስትሪ ሊኖር የሚችለው እና ያለንን እምቅ የቆዳ ሃብት መጠቀም የምንችለው የቁም እንሰሳት ሃብታችን ላይ በትክክል መስራት ስንችል ብቻ ነው፡፡ ለዚሁም የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን በተለይም በአርብቶ አደር አከባቢ በተገቢው የእንስሳት አረባብ ዘዴ መተግበር ሲቻል ነው፡፡ የዚህ አገልግሎት ትግበራ በዘመናዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ላይ እና እንሰሳቱ በቁም እያሉ መደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የግብርናው ዘርፍ አለመዘመን እና በተለይ በአርብቶ አደር አከባቢ ለሚኖሩ የህብረሰብ ክፍላችን ገበያ ተኮር የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን በአግባቡ ተደራሽ አለመሆን በእንሰሳቱ ዘርፍ ያለንን እምቅ ሃብት ለመጠቀም ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት እንደሚገባ ዳይሬክተሩ በአጽንኦት አስረድተዋል፡፡ ይህንን አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ በአርብቶ አደር አከባቢዎች ጠንካራ ሚና መጫወት የሚችል አመራር እና ባለሙያ ማፍራት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡

ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የእንሰሳቱ የግብይት ሂደት ነው፡፡ የእንሰሳት የግብይት ስርዓቱ አርብቶ አደሩን፣ ከፊል አርብቶ አደርና አርሶ አደሩን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ ማለት አርብቶ አደሩ እንሰሳቱን በአቅራቢያው በሚገኙ የገበያ ማዕከላትን ተጠቅሞ መሸጥ የሚያስችለው ስርዓትን መዘርጋት እንሰሳቱን ከእንግልት መታደግ መሆኑም ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

በእርድ ወቅት ለጥሬ ቆዳና ሌጦ ሃብታችን ጥንቃቄ አለመስጠት ከቆዳና ሌጦ ሃብታችን ማግኘት የሚገባንን ጥቅም እንዳናገኝ ያደረገን ሌላኛው ችግር ነው፡፡ ከእንሰሳት የምናገኘው ዋንኛው ምርት ስጋ ቢሆንም ከስጋ በተጓዳኝ በእርድ ወቅት በሰፊው የሚመረተው ጥሬ ቆዳና ሌጦም ቀላል የማይባል ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው ሀብት ነው፡፡ ሆኖም አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በእርድ ወቅት ለስጋ የሚደረገውን ጥንቃቄ ያህል ለቆዳና ሌጦ ጥንቃቄ ተሰጥቶታል ማለት አይቻልም፡፡

በተለይ የበግና የፍየል እርድ የሚከናወነው በባህላዊ መንገድ በየቤቱና በየሰፈሩ ውስጥ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በዓመት በዓል ወቅት በሚደረግ ዕርድ ላይ ለቆዳና ሌጦ ልዩ ትኩረት እየተጠው ባለመሆኑ በበዓል ወቅት የሚቀርበው የቆዳ ምርት በአብዛኛው በዕርድና ከዕርድ በኃላ ባለው ተገቢ ያልሆነ አያያዝ ሃገሪቱ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እያገኘች አይደለም፡፡

በዚህም የተነሳ በበዓላት ማግስት በበርካታ አካባቢዎች ቆዳ በመጣሉ የተነሳ ለአካባቢ ብክለት መንስኤ እየሆነ ይገኛል፡፡ ምንም እንኳን በሃገራችን ዘመናዊ ቄራዎች በየአቅራቢያው ባይኖሩም ባሉት ቄራዎች እንኳን ተጠቅመን በባህላዊ መንገድ የሚከናወኑ ዕርዶችን ማስቀረት ብንችል እና ከእርዱ በኋላ ቆዳው ሳይበላሽ በጥንቃቄ በማዘጋጀት በየአከባቢው ለሚገኙ የቆዳ ተረካቢዎች ማስረከብ ቢቻል ይህንን ችግር ለመቅረፍ ሁነኛ መፍትሄ መሆኑ አጠያያቂ ጉዳይ አይደለም፡፡

ለቆዳ እና ለቆዳ ውጤቶች ማዘጋጃ የሚሆኑ የኬሚካልና የጨው አቅርቦት እጥረትና የዋጋ መናር ችግር ሃገራችን ከቆዳ ሃብት ማግኘት የሚገባትን አንጻራዊ ተጠቃሚነት እንዳታገኝ ያደረጋት አንዱ ምክንያት ነው፡። ይህንን ትልቅ ተግዳሮት ለመቅረፍ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ባደረገው መጠነ ሰፊ ውይይት ለቆዳ ፋብሪካዎች የውጪ ምንዛሬ ችግር እንዳይገጥማቸው ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

የቆዳ እንዱስትሪዎቻችን ዘመናዊ አለመሆንና ያሉትም በሙሉ አቅማቸው አለማምረታቸው የቆዳና ሌጦ ሀብታችንን በሚፈለገው መጠን እንዳንጠቀም ከሚያደርጉን ምክንያቶች ውስጥ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ሰፊ ርቀት የሄደ ቢሆንም አሁንም በቀጣይ የሚቀሩ በርካታ የቤት ስራዎች እንዳሉ ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ተግዳሮቶች ያለንን የቆዳ ሃብት እንዳንጠቀም ካደረጉን ምክንያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ እነዚህ ማነቆዎች ለመቅረፍ በቆዳ እና በቆዳ ውጤቶች ዘርፍ ላይ ካሉ ተዋናዮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን ፈጥሮ በትኩረት መስራት ተገቢ መሆኑን አቶ ዴስነት ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ የጋራ የምክክር መድረክ ማካሄድ፣ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመለየት ለችግሮቹ መፍትሄ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ጥናቶችን ማካሄድና በተገኙ የጥናት ውጤቶች ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ በተያያዘ መልኩ በአሁኑ ወቅት የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንሲቲትዩትና በኢትዮጵያ ቆዳ አቅራቢዎች ማህበር በኩል የተሻለ እንቅስቃሴ እየተደረገ ቢሆንም በቀጣይ በርካታ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች መኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ የቆዳ ሃብታችንን በአግባቡ ተጠቅመንና ወደ ገንዘብ ቀይረን ሃገራችን ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሁሉም የጋራ ርብርብ ያስፈልጋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.facebook.com/Ethiopia-Ministry-of-Trade-and-Industry

# ለኢትዮጵያ ባንኮች አፍሪ ኤግዚም ባንክ ግማሽ ቢሊዮን ዶላር ብድር ሊሰጣቸው ነው ተባለ

የአፍሪካ ኢምፖርት-ኤክስፖርት ባንክ (አፍሪ ኤግዚም ባንክ) ለኢትዮጵያ ባንኮች ግማሽ ቢሊየን ዶላር ብድር ለማቅረብ ማጽደቁን ይፋ አደረገ።

የአፍሪካ ኢምፖርት-ኤክስፖርት ባንክ (አፍሪ ኤግዚም ባንክ) ለአህጉራዊ ንግድ ትስስርና ልማት የማጎልበት ዓላማ በማንገብ በአውሪፓዊያኑ 1993 በግብጽ – ካይሮ የተቋቋመ የፋይናንስ ተቋም ነው።

ኢትዮጵያ መስራችና ባለድርሻ የሆነችበት አፍሪካ ኤዝዚም ባንክ 51 የአፍሪካ አገራት በአባልነት አቅፏል።

የአፍሪ ኤግዚም ባንክ የደንበኞች ግንኙነት ዓለም አቀፍ ዳይሬክተር ረኔ አዋምበንግ እንዳሉት፤ ባንኩ ከሌሎች አፍሪካዊ ባንኮች ጋር መወዳደር ሳይሆን በፋይናንስ ዘርፍ የአፍሪካን ችግር በአፍሪካ ለመፍታት ይሰራል።

እስካሁንም ከ25 ቢሊዮን ዶላር በላይ በአፍሪካ ንግድ ፋይናንስ ዘርፍ ለፕሮጀክቶች ድጋፍ ማድረጉን ተናግረዋል።

ላለፉት ዓመታት በአፍሪካ መንግስታት ፋይናንስ ዘርፍ ትልቅ ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን ገልፀው፤ በኮቪድ-19 ወረርሽኝም ከሦስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ድጋፍ ማቅረቡን ተናግረዋል።

አሁንም ተጨማሪ ለጸረ ኮቪድ ክትባት ግዥ የሚውል ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ገንዘብ ለማቅረብ ከአፍሪካ ህብረትና ከሌሎች ባለደርሻ አካላት ጋር በጋራ እየሰራ መሆኑንም አመልክተዋል።

የኢትዮጵያ ባንኮች በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ባስከተለው ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ውድቀት ውስጥ ሆነው በፈጣን ለውጥ ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

ከ110 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ያላት ኢትዮጵያ በተለይም የአፍሪካ ቀንድ ምቹ ገበያ እንደሆነች ገለጸው፤ ባንኩ በፓን አፍሪካ ማዕቀፍ የአፍሪካ አገራት መካከል የሚደረግ የንግድ ልውውጥ እንዲሰጥ ድጋፍ እንደሚያደርግ አብራርተዋል።

ባንኩ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለተመታው የአፍሪካ ኢኮኖሚ ማገገሚያም ሶስት ቢሊዮን ዶላር ለባንኮች ድጋፍ መስጠቱን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የተዘጋጀው መድረክ ዓላማም ከኢትዮጵያ የፋይናንስ ተቋማት ጋር በጋራ ለመስራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ለመምከር ስለመሆኑ አንስተዋል።

ይህም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ዕድገት አጀንዳዎች ማስፈጸም በሚያስችሉ ዘርፎች ለመደገፍ በኢትዮጵያ ለሚገኙ ባንኮች 500 ሚሊዮን ዶላር ብድር ለመስጠት ባንኩ ውሳኔ ማሳለፉን ተናግረዋል።

ባንኩ ካሁን በፊት በኢትዮጵየ በአጠቃላይ በተለያዩ ዘርፎች ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ድጋፍ ማድረጉን አስታውሰዋል።

በመስከረም መጨረሻም ሁሉም ሂደቶች ከባንኮች ጋር ከተፈጸሙ በኋላ ብድሩ እንደሚቀርብም ግምታቸውንም ገልጸዋል፤ ለእያንዳንዱ ባንክ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚቀርብላቸውም አሳውቀናል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ በበኩላቸው፤ ባንኩ በአፍሪካ አገራት መካከልና አፍሪካን ከዓለም ጋር ያላትን ንግድ ለማሳለጥና በንግድ የማስተሳሰር ዓላማ ይዞ መቋቋሙን ተናግረዋል።

ከአፍሪ ኤግዚም ባንክ በርካታ የአፍሪካ አገራት ብድሮችና ሌሎች አገልግሎቶችን ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸው፤ ኢትዮጵያ መስራች በሆነችበት ኤግዚም ባንክ እስካሁን ተጠቃሚ እንዳልነበረች ገልጸዋል።

አፍሪ ኤግዚም ባንክ ለአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ትስስር ስኬት አንዱ አሳላጭ ተቋም መሆነን ገልፀው፤ እንደሌሎች ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ሁሉ በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ እንዲከፍትም ጥያቄ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከአፍሪካ የገቢና ወጪ (ኢምፖርት ኤክስፖርት) ባንክ ጋር በቅርበት ለመስራት ቁርጠኛ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ እስካሁን ከባንኩ ጋር ተጠቃሚ ያለሆነችው የኢትዮጵያ ባንኮች ከውጭ ባንኮች መበደር እንዳይችሉ የሕግ ከለላ ስለነበር መሆኑን አንስተዋል።

ከሕግ ማዕቀፍ ባሻገር የኢትዮጵየ ባንኮች ከአፍሪካ የፋይናንስ ተቋማት በጋራ ለመስራት ልምድ ደካማ እንደነበር ገልጸው፤ በቀጣይ ግን "ይህን እድል ለመጠቀም እንሰራለን" ነው ያሉት።

የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና እንዲሳለጥ ከሚያደርጉት አካላት አንዱ አፍሪ ኤግዚም ባንክ መሆኑን ተናግረዋል።

በቀጣይ ግን ባንኩ የሚሰጣቸውን አገልግሎት ኢትዮጵያ መጠቀም እንደምትሻ በመግለጽ፤ ለባንኮች የሚሰጠው ግማሽ ቢሊዮን ዶላር ብድርም በተመለከተም ከባንኮች ጋር ሰፊ ውይይት እንደሚደረግ ነው ያመለከቱት።

የኢትዮጵያ ባንኮች ከውጭ ባንኮች ገር መስራታቸው በተለይ ለኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለማቃለል ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ገልጸዋል።

በመሆኑም የአፍሪ ኤግዚም ባንክ የብድር አቅርቢነት ውሳኔ ከዚፍ አኳያ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ገልጸው፤ ሌሎች የውጭ ባንኮችም በቅረበት እንዲሰሩ እንደሚበረታቱ ተናግረዋል።

የባንኩ የስራ ሃላፊዎችና የኢትዮጵያ ባንኮች አመራር አባላት የሦስት ቀናት የስልጠናና ምክክር መድረክ በአዲስ አበባ አካሂደዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethioliving.com/featured/ለኢትዮጵያ-ባንኮች-አፍሪ-ኤግዚም-ባንክ-ግ/

# የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በወቅታዊ የዘርፉ ችግሮች ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር አደረገ

የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ የዘርፍ ኢንዱስትሪዎችን ችግር በመፍታት በአገሪቱ ላይ እየተሰሩ ያሉ የኢኮኖሚ አሻጥሮችን መቀልበስ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ከኢንዱስትሪ ባለሀብቶች፣ ከአስመጪዎችና ከዘርፍ ማህበራት ጋር ምክክር አድርገዋል፡፡

ውየይቱ ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪን በማድረግ የህብረተሰቡን የኑሮ ውድነት የሚያንሩ ህገ ወጥ ነጋዴዎችን በጋር መካላከል ስለሚቻልበት ሁኔታዎች ላይ ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር ምክክር ማድረግን ዓላማ ያደገ መሆኑን በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር የሆኑት አቶ አስፋው ረጋሣ ገልጸዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ ህገ-ወጥ ንግድ፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ንዑስ ዘርፉን እየተፈታተኑ ያሉ ዋና ዋና ወቅታዊ ችግሮች መሆናቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ብረት ብረት ኢንዱስትሪ የኢንዱስትሪዎች ማህበር ስራአስኪያጂ አቶ ሰለሞን ሙሉጌታ ተናግረዋል፡፡

በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የተቋቋመ ግብረ-ኃይልም አስተማማኝ አቅርቦት እንዲኖር፣ ህገ-ወጥ ንግድ ለመከላከልና በየደረጃው ጉዳዩ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጋር እየተወያየ መሆኑን አቶ ሰለሞን ሙሉጌታ አክለዋል፡፡

በአገር ደረጃ ያለውን የኢኮኖሚ አሻጥርና በንዑስ ዘርፉ ያለውን ችግር መፍታት የሚቻለው ቅንጂታዊ አሰራሮችን በማጠናከር ከባለድርሻ አካላት ከአምራች ኢንዱስትሪው፣ ከዘርፍ ማህበሩ፣ከኢንስቲትዩትና ከሚኒስትር መ/ቤቱ የሚጠበቁ ተግባራት በአግባቡ ማከናወን ሲችሉ መሆኑም በውይይቱ ላይ ተገልጿል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.facebook.com/Ethiopia-Ministry-of-Trade-and-Industry

## የኢትዮጵያና ኬኒያ የሞያሌ አንድ ድንበር አገልግሎት የንግድ ሥራ ፍሰቱን ቀልጣፋ፣ አዋጭና ውጤታማ እንደሚያደርገው ተገለጸ

የኢትዮጵያና ኬኒያ የሞያሌ በአንድ ድንበር የሚያልቅ የጉምሩክ አገልግሎት መጠቀም “የንግድ ሥራ ፍሰት ቀልጣፋ፣ አዋጭና ውጤታማ” እንደሚያደርገው ተገለጸ።

ይህ የተገለጸው የኢትዮጵያና ኬኒያ መንግስታት የሞያሌ አንድ አለቅ የድንበር አገልግሎት ማዕከል የአሰራር መመሪያ ሂደትን ለመተግበር የሚያስችል ስምምነት በአዲስ አበባ በተፈራረሙበት ወቅት ነው።

ስምምነቱን የጉምሩክ ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታ እና የኬንያ የአገር ውስጥ ደህንነት ዋና ፀሐፊ ዊልሰን ኒጂጋ ፈርመዋል።

ስምምነቱ በሁለቱ ሃገራት መካከል የሚካሄደውን የንግድ ትብብር ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን እንደሚያስችል ተጠቅሷል።

የሞያሌ የጋራ የመተላለፊያ ጣቢያ የሀዋሳ – ሀገረ ማሪያም – ሞያሌ መንገድ አካል ሆኖ የተሠራ ነው፡፡

የጉምሩክ ኮሚሽነር አቶ ደበሌ በዚሁ ወቅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያና ኬንያ ዘመን የተሻገረ ወዳጅነት አላቸው፡፡

በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው የንግድ ግንኙነት ካላቸው አቅም አኳያ ሲታይ አነስተኛ መሆኑን ጠቁመው፤ መመሪያው ይህንኑ ለማስተካከል ከፍተኛ አቅም እንደሚፈጥር አረጋግጠዋል፡፡

የጋራ መተላለፊያ ጣቢያው በድንበር ላይ የሚደረገውን የተንዛዛና ረጅም የመተላለፊያና የይለፍ ፈቃድ አሰጣጥ ቀልጣፋ ስርዓት የሚፈጥር መሆኑን አመልክተው፤ በሁለቱ አገራት መካከል ያለውን “የንግድ ሥራ ፍሰት ቀልጣፋ፣ አዋጭና ውጤታማ ያደርገዋል” ሲሉ ኮሚሽነሩ ተናግረዋል፡፡

ኮሚሽነር ደበሌ በተጨማሪ እንደተናገሩት፤ አሁን ላይ በሀገራቱ መካከል ያለው የንግድ ልውውጥና የሸቀጦች ዝውውር ስብጥር በከፍተኛ መጠን ጨምሯል፡፡

የኬንያ የአገር ውስጥ ደህንነት ዋና ፀሐፊ ዊልሰን ኒጂጋ በበኩላቸው፤ ስምምነቱ የሁለቱን ሀገራት ድንበር በጋራ ለመቆጣጠር ጠቃሚ መሰረት የተጣለበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ሁለቱ ሀገራት በጋራ መተላለፊያው በመጠቀም በድንበር ላይ ያለውን እንቅስቃሴ በአንድ ማዕከል ለማከናወን እንደሚያስችላቸውም ጠቅሰዋል፡፡

የተደረገው ስምምነት በድንበር አካባቢ የሚከናወነውን የሁለቱን ወዳጅ ሀገራት የንግድ ዝወውር በከፍተኛ መጠን የሚያሳድግና የሚያሳልጥ መሆኑንም ዋና ፀሐፊው ተናግረዋል፡፡

ስምምነቱ የድንበር ዝውውሩን ሂደት ቀላልና ቀልጣፋ ለማድረግ ከማስቻሉ በላይ ጊዜን ለመቆጠብ እንደሚረዳ ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል፡፡

የጋራ የመተላለፊያ ጣቢያ ነጋዴዎች ፣ሰዎች ወይም ተሽከርካሪዎች ድንበር ሲያቋርጡ በሁለት ሀገራት ጉምሩክ፣ ኢሚግሬሽን፣ የጤና የመተላለፊያ፣ ደረጃ መዳቢ አልፈው እንዲሄዱ ያስችላቸዋል፡፡

ከዚያም በመዳረሻ ሃገር በተገነባው የመተላለፊያ ጣቢያ ብቻ በመቆም አስፈላጊውን የመግቢያና የመውጫ አገልግሎት በጣቢያው በሚሰሩ የሁለቱ ሀገራት ባለሙያዎች ዘንድ ማግኘት እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡

የሀገራቱን የድንበር ነክ ጉዳዮች የሚቆጣጠሩ ሰራተኞች የተቀናጀ የድንበር አስተዳደር ስራዎችን በተሳካ መልኩ መተግበር እንዲችሉ አቅም ይፈጥራል ተብሏል፡፡

የጋራ መተላለፊያ ጣቢያው የህዝብ ለህዝብ ትስስሩንና የጋራ ልማትን በማጠናከር የሀገራቱን ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ግንኙነት የበለጠ እንደሚያሳድገው በስምምነቱ ላይ ተገልጿል፡፡

የአሰራር ሂደት መመሪያ ስምምነቱ ባሳለፍነዉ ዓመት ሰኔ 1 ቀን አገልግሎት መስጠት የጀመረውን የሞያሌ አንድ – አለቅ የድንበር አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ወደስራ እንደሚያስገባ ተመላክቷል፡፡

የሞያሌ አንድ አለቅ የድንበር አገልግሎት ህዳር 30 ቀን 2013 ዓ.ም በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ እና በኬንያው ፕሬዝዳንት ኡሁሩ ኬንያታ ተመርቆ ሥራ መጀመሩ የሚታወስ ነው።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethioliving.com/featured/የኢትዮጵያና-ኬኒያ-የሞያሌ-አንድ-ድንበር/

## ኮሚሽኑ በአሸባሪው ህወሓት የወደሙ ኢንተርፕራይዞች መልሶ ለማደራጀት ትኩረት እንደሚሰጥ አስታወቀ

ለሥራ ፈላጊዎች የሥራ ዕድል ከመፍጠሩ በተጓዳኝ በአሸባሪው ህወሓት የወደሙ ኢንተርፕራይዞችን መልሶ ለማደረጀት ትኩረት እንደሚደረግ የፌደራል ሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን አስታወቀ።

የፌዴራልና ክልል አመራሮች የተሳተፉበት የሥራ ዕድል ፈጠራ የውይይት መድረክ በባህር ዳር ከተማ ተካሄዷል።

የሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽነር አቶ ንጉሱ ጥላሁን በወቅቱ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ በተስፋና በስጋት ውስጥ ሆና ባሳለፈችው 2013 ዓ.ም በሥራ ዕድል ፈጠራ የተሻለ አፈጻጸም ነበረ።

“በርካታ እንቅፋቶች ቢገጥሙም ችግሮችን በመቋቋም ለ3 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል” ብለዋል።

አሸባሪው ህወሓት በወረራቸው አካባቢዎች የተገነቡ የሥራ እድል ፈጠራ ተቋማትን ማውደሙን የገለጹት አቶ ንጉሱ፤ ድርጊቱ የሥራ ዕድል ፈጠራ እንቅስቃሴውን ፈተና ውስጥ እንዲገባ ያደረገው መሆኑን ተናግረዋል።

ላለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የሴቶች የስራ ዕድል ጠጠቃሚነት ድርሻ 35 በመቶ ብቻ በመሆኑ ሴቶች ከወንዶች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በተያዘው የበጀት ዓመት ነባር ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከርና ለአዳዲስ ሥራ ፈላጊዎች የሥራ ዕድል በመፍጠር 3 ሚሊዮን ዜጎችን በዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል።

“የዜጎች የሥራ ዕድል ፈጠራ የሁሉንም አካላት ጠንካራ ድጋፍና እገዛ ይፈልጋል” ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ለዚህም ባለድርሻ አካላት ከመቼውም ጊዜ በላይ ለዘርፉ ትኩረት እንዲሰጡ ጠይቀዋል።

በምክትል ርዕሰ መስተዳደር ማዕረግ የአማራ ክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሃላፊ ዶክተር ሙሉነሽ አበበ በበኩላቸው በክልሉ የህወሓት አሸባሪ ቡድን በከፈተው ጦርነት ከ18 ሺህ 900 በላይ ኢንተርፕራይዞችና የቴክኒክ ሙያ ኮሌጆች መውደማቸውን ገልጸዋል።

“ሰላም ከማስከበሩ ተግባራት ጎን ለጎን የወደሙ ኢንተርፕራይዞችን፣ ከሥራ ውጭ የሆኑ ተቋማትን ማቋቋም ትልቁና የመጀመሪያ ስራ መሆን አለበት” ብለዋል።

ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ አየለች እሸቴ ሥራ አጥ ዜጎችን በመመዝገብ ስራ ለማስያዝ ከባለድረሻ አካላት ጋር እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል

ክፍት የስራ ቦታዎችን የመመዝገብና ሥራ ፈላጊውን የማገናኘት ሥራዎች በሚኒስቴሩ እንደሚከናወኑ ጠቅሰው፣ በተለይም በውጭ ሀገር የሥራ እድሎችን የማመቻቸት ሥራ እየሰሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በዚህም ከጥቅምት ወር 2013 ዓ.ም ጀምሮ ለ50ሺህ ዜጎች በውጭ አገራት የሥራ ዕድል መፈጠሩን አስረድተዋል።

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሣኒ ረዲ ፈተና የበዛበት ያለፈው በጀት ዓመት የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ ጥሩ አፈጻጸም እንደታየበት ገልጸዋል።

የግብርና ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት በገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራ የፋይናንስ እና የመሬት አቅርቦትን በማስተሳሰር በኩል የድርሻውን እንደተወጡም አስረድተዋል።

ተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethioliving.com/ ኢኮኖሚ/በአሸባሪው-ህወሓት-የወደሙ-ኢንተርፕራይ/

## በተያዘው በጀት ዓመት የገበያ ማረጋጋት ልዩ ትኩረት ይደረግበታል

በተያዘው በጀት ዓመት የገበያ ማረጋጋት ልዩ ትኩረት ይደረግበታል

በተያዘው በጀት ዓመት በገበያ ማረጋጋት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በልዩ ትኩረት የሚሰራ መሆኑን የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት አስታወቀ።

ድርጅቱ የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀምን እና በ2014 የያዘውን ዕቅድ በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር መክሯል።

የድርጅቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ የሺመቤት ነጋሽ፤ ድርጅቱ ከዚህ

በፊት ከነበሩበት የተለያዩ ችግሮች ተላቆ የተሻለ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ተናግረዋል።

በመሆኑም የኢንዱስትሪ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና ገበያን ለማረጋገት እየሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የፍጆታ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ገበያ ማረጋጋትና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ዋነኛው ትኩረቱ መሆኑንም ዋና ስራ አስፈጻሚዋ አንስተዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት አግሮ ፕሮሰሲንግ፣ በጨርቃጨርቅ እና አልባሳት፣ በቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ ኮንስትርክሽንና ኬሚካል ዘርፎች አቅርቦት ላይ በትኩረት እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

የድርጅቱን ተልኮ በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል እና ባለድርሻ አካላትን በሚገባ ለማገልገል ዝግጅት መደረጉን ገልጸው፤ “ከግዥም ሆነ ከአቅርቦት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት እንሰራለን” ብለዋል።

የግብይት ስርአቱን ዲጂታል በማድረግ ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ብልሹ አሰራርን ለመቆጣጠር እንደሚጥር ጠቁመዋል።

በ2013 በጀት ዓመት የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት 2 ነጥብ 3 ቢሊየን ብር ተመድቦ ለተለያዩ የምግብና መሠረታዊ ፍጆታዎች ግዥ መዋሉን ጠቅሰዋል።

“በ219 ሚሊየን ብር ሲሚንቶ፣ ከ23 ሚሊየን ሊትር በላይ ፓልም ዘይት እና 6 ሚሊየን ሊትር ፈሳሽ ዘይት እንዲሁም ከ1 ሚሊየን ኩንታል በላይ ስኳር በቅናሽ ዋጋ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ተደርጓል” ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ ድርጅቱ ከ3 ነጥብ 1 ቢሊየን ብር በላይ ገቢ ማግኘቱንም ተናግረዋል።

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴዔታ አቶ ተካ ገብረየስ ድርጅቱ ያለበትን ውስብስብ ችግሮች በመፍታት ገበያን ለማረጋጋት እና የኢንዱስሪ ምርቶችን ለማቅረብ እያደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ መሆኑን ገልጸዋል።

በውይይቱ ላይ የተሳፉ ባለደርሻ አካለት በበኩላቸው በድርጀቱ ያለው መሻሻል የሚበረታታ መሆኑን ተናግረው፤ በቀጣይ የግብዓት አቅርቦትም ሆነ የገበያ ማረጋጋት ላይ ስራ ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት አመልክተዋል።

ተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethioliving.com/ኢኮኖሚ/በተያዘው-በጀት-ዓመት-የገበያ-ማረጋጋት-ል/

## የኢትዮ–ኬንያ በኢነርጂ ዘርፍ ላይ ያተኮረ የሁለትዮሽ ውይይት ተካሄደ

ኢትዮጲያና ኬንያ በኢነርጂ ዘርፍ ላይ ያተኮረ የሁለትዮሽ ውይይት አካሂደዋል።

ኢትዮ – ኬንያ ለኃይል መሰረተ ልማት ዝርጋታ ግዙፍ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰሳቸው ተገልጿል፡፡

የሁለቱ አገራት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሮች አማካኝነት ዛሬ የተጀመረው ውይይት ለሁለቱ አገራት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለውን የኢነርጂ መሰረተ ልማት ግንባታ ሂደትን ለማፋጠን በሚያስችሉና በሌሎች ቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ታውቋል።

የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ስለሺ በቀለ እና የኬንያ ኢነርጂና ነዳጅ ሚኒስትር ሚስተር ቻርለስ ኬተር ከልዑካን ቡድኖቻቸው ጋር በመሆን ውይይት አድርገዋል።

ሚኒስትሮቹ በውይይቱ ላይ እንደገለፁት፤ ሁለቱ አገራት ለኃይል መሰረተ ልማት ዝርጋታ ግዙፍ መዋዕለ ንዋይ አፍስሰዋል።

ከአንድ ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ የሚረዝመው የሁለቱ አገራት የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ጋር ሊያስተሳስር የሚችል ግዙፍ ፕሮጀክት ነው፡፡

ይህ ፕሮጀክት ተገንብቶ አገልግሎት ሲጀመር ለሁለቱ አገራት ኢኮኖሚያዊ እድገት ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው ሚኒስትሮቹ ገልፀዋል።

በኢትዮጵያ በኩል የተዘረጋው የ412 ኪሎ ሜትር የከፍተኛ ኃይል ተሸካሚ መስመርና የዲሲ ኮንቨርተር ማከፋፈያ ጣቢያ ግንባታ ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ የሙከራና ፍተሻ ስራ ተከናውኖበታል፡፡

በተመሳሳይ በኬንያ በኩል መዘርጋት ካለበት 633 ኪሎ ሜትር ውስጥ 30 ኪሎ ሜትር ብቻ መቅረቱ በውይይቱ ላይ ተጠቅሷል።

በመሆኑም ቀሪውን ግንባታ በቀጣይ አንድ ወር ለማጠናቀቅ እየተሰራ መሆኑን የኬንያ ኢነርጂና ነዳጅ ሚኒስትር ቻርለስ ኬተር አስታውቀዋል።

የሁለትዮሽ ውይይት የኃይል ማስተላለፊያ መስመሩ ሲጠናቀቅ የሙከራ ስራ በሚጀመርበት ሁኔታ ላይ ለመምከርና ቀደም ሲል የተፈረመው የኃይል ሽያጭ ስምምነት ላይ ያልተጠናቀቁ ጉዳዮችን ለማጠናቀቅ ነው ተብሏል።

ተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethioliving.com/featured/የኢትዮ-ኬንያ-በኢነርጂ-ዘርፍ-ላይ-ያተኮ/

ዋና አዘጋጅ፡-

ደበበ አበበ

አዘጋጅ፡-

ዮሴፍ ተሾመ

ካሜራ፡-

ያሬድ አባቡ


አድራሻ፡-

ስልክ-፡- +251-115-54-09-93

ፋክስ፡-+251-011-5517699

ድረ-ገጽ፡-
www.ethiopianchamber.com

Facebook:
https://www.facebook.com/
EthiopianChamber

Twitter:
https://twitter.com/
EthiopiaChamber

Telegram:
t.me/ethiopiachamber


## ECCSA Resource Center

Ethiopian Chamber of Commerce & Sectoral Associations (ECCSA) Resource Center has stated giving service to member. The center is located at the head quarter of ECCSA.

It is a unit dedicated to serve the business community, its members and staffs with a range of timely and cost-effective information services which will enhance the decision-making process and competitiveness of the chamber system management and the business community.

It is also a WTO (World Trade Organization) Reference Center for the private sector, to enable business community to access online trade data and WTO-related documents on a continuous basis, to help identify market niches for the export of their products and services.

The center works on the principle of the 5Rs: providing the Right information to the Right person at the Right time in the Right quantity and Right quality.

The Center's Services

Reference, Resources Loan & Interlibrary Loan Services

Internet & Electronic Resource Services

Support on information searching

Reprographic Service

Advising users on reference materials available in resource center.

Types of Materials in the Center

Books, Periodicals, Journals, Magazines

Audio and Video CD collections

E-Books & Publications

Business & Economic Statistics & Databases

Access to international organization's online information (WTO, ITC, UNCTAD, World Bank, PACCI, WCO, etc.)

For further information:

Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations

ECCSA Resource & WTO Reference Center

Mexico Square, ECCSA Building

Ground Office , Room No. 13/14

Open to public Monday-Friday from 2:30 am to 5:00 pm

Tel: 251-115514005

Mob. 0966038499

Fax: 251-115517699

# የግልግል አገልግሎት



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/95 አንቀጽ 5(6) መሰረት በንግድ ማህበረሰቡ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እንዲፈታ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሰረት አለመግባባቶችን በፈጣን እና ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲፈታ ከማድረጉም በላይ ለባለ ጉዳዮች አመቺ እንዲሆን ቅዳሜንም ጨምሮ ዓመቱን ሙሉ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑን የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ እንድትሆኑ ስንጠይቅ የንግድ ማኅበረሰቡን ለማገልገል ያለንን ቁርጠኝነት በመግለጽ ነዉ፡፡

ለበለጠ መረጃ ፡- ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘዉ የንግድ ምክር ቤት
ሕንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 15 በአካል በመቅረብ
ወይም
በስልክ ቁጥር +251 115 311015 በመደወል ማነጋገር ትችላላችሁ፡፡

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የግልግል ማዕከል**